የበለሳው ፊታውራሪ ነጋሽ ስማቸውን አደሱ። ከመውደቃቸው በፊት እስከመጨረሻዋ ደቂቃ ድረስ እሌ የማይባል ጀግና መሆናቸውን አስመስከሩ። ለሁልጊዜም ጀግና እንደሆኑ ይኖራሉ።

ጣልያኖች በቁጥር እጥፍ ቢሆኑም የኢትዮጵያውያኑ ቀዳሚ ጦር ያሉበት ቦታ እንዳይንቀሳቀሱ አድርጓቸዋል። ጠላት ወደፊት መጓዝ አልቻለም እንዲያውም ለትንሽ ርቀት ወደኋላ ለማፈግፈግ ተገዷል።

አመሻሽ ላይ ወደፊት ተጓዝንና ከአፍ ጋጋ ማለፊያ አራት ኪሎ ሜትር ርቀት ቦታ ደረስን። በዚያ አካባቢ ያሉ ዋሻዎች ብዛት አልነበራቸውም ግን ሰፋፊ ነበሩ። ከመሬት በታች የሆነ አንድ ከፍል ውስጥ መጠለያ አደረግን የዚህ መጠለያ መግቢያው መሀል ሜዳ ላይ ከትልቅ ዛፍ ስር ነበር። ሁለተኛው መግቢያ ደግሞ ወደ ገደል ነው የሚወስደው። ቦታው ውስጥ የነበርነው ወደ ሁለት ሺ ሰዎች እንሆናለን ግን ከርን ለከርን አልተገፋፋንም። ፊታውራሪ ሙላውና የራስ እምሩ ፊታውራሪ ከንፈ ፊታውራሪ ነጋሽ የሞቱበትን ቦታ መልሰው እንዲይዙ ታዘዙ።



# ምዕራፍ አሥራ ሰባት

## ቅዱስ ጊዮርጊስ አልጠበቀንም

የካቲት ሀያ ሶስት ነጋ። የአድዋ ድል አርባኛ አመት ነበር። እንደዛን ጊዜም ዛሬ እሁድ ነው። ጨለማን ተገን አድርገው የጠላት ወታደሮች ወደፊት በመጓዝ ጋራውን አቃበ ሰእት፣ አዲ ሀመልማል እና ሰለህለሀን ይዘዋል። እነዚህ ቦታዎች ደግሞ ጎን ለጎን ነው ያሉት። ከመጨረሻው ቦታ በምሥራቅ በኩል ደግሞ አዲስ ሬጅመንት በጥዋት ቦታውን ያዘ። አሁን ከአክሱም በረድፍ የሚመጡ የጭነት መኪኖችን እናያለን። ተጨማሪ ወታደር ሰንቅና ትጥቅ ነው ይዘው የሚመጡት። እሁኑኑ ለማጥቃት እንዳሰቡ ምንም ምልክት አይታይም።

ከቀኑ ወደ መሀል ላይ በመጣ ዜና ደግሞ ሞተረኛ የሆነ የጣልያን ጦር በመረብ በኩል አድርጎ አዲ እዞ ተሻግሮ እየተጓዘ እንደሆነ ሰማን። ግልፅ ሆኖ እንደሚታየው ከኋላችን ሆነው ሊያጠቁን ፈልገዋል። ወይም ደግሞ መሸሻ መንገዳችን ከኋላ በኩል በምዕራብ አድርገው በቆየሳ ተራራ ዙሪያ መዝጋት ፈልገዋል። ሁለቱ የጣልያን እስረኞች ሳያጋንኑ ለመናገራቸው ይህ በቂ መረጃ ነበር። እኛን ወደ ወጥመድ ሰበው በመከበብ ሙሉ በሙሉ ለመደምሰስ ፈልገዋል።

በሚያስተማምን መልከተኛ በኩል ራስ እምሩና ደጃች አያሌው ሙሉ ቀን መልከት ሲለዋወጡ ዋሉ። ደጃች አያሌው ጠላት ሳይጠናከር እሁኑኑ ማጥቃት ፈልገዋል። ውነት ነው ቀኑ ሁለት በአል ነበረው እሁድም እና ቅዱሰ ጊየርጊሰም ነበር። ግን ደጃዝማች “በችግር ምክንያት መደረግ ያለበት ነገር ሲኖር ህግና ልምድ አይከበርም” አሉ።

ነገር ግን ራሰ እምሩ እርግጠኛ አልነበሩም እና በማታ መንቀሳቀሰ ነው የሚሻለው ብለው ነው ያሰቡት። እለዚያ እንዴት ተብሎሰ የአየር ጥቃቱን ማምለጥ ይቻላል? በዚህ እንኳን ውነት ነው ትክከል ነበሩ።

የደኞች አያሌው ልጅ ፊታውራሪ ዘውዱ በምሥራቅ በኩል የሚገኝ ማለፊያ በር እንዲጠብቁ ተልከው ወደ ማለፊያው ሲጓዙ የአየር በምብ ጥቃት ደረሰባቸው፡፡ አራት መኮንኖችና ሃምሳ ወታደሮቻቸው በገደል ውስጥ ገብተው ተሰውረዋል፡፡ አነሰ ያለ ጉድጓድ ውስጥ ዘለው በመግባት ማምለጣቸው ፊታውራሪው እራሳቸው ዕድለኛ ነበሩ፡፡ በተአምር ነው የዳኑት፡፡ ወታደሮቹም ሰለተበታተኑ ማታ ነው ማሰባሰብ የተቻለው፡፡

በዚያን እለት ጣልያኖቹ ትልልቅ በምብ ጣይ እውሮፕላኖቻቸውን በሙሉ ነው ያሰለፉት፡፡ እንስሶች እንደ መጀመሪያው ቀን ሰላልተጠበቁ በገፍ ነው ያለቁት፡፡ ሜዳው ዳገቱ ሁሉም ቦታ ይነድ ስለነበር ሙቀቱ የሚቻል አልነበረም፡፡ ያልበንም ነበር፤ ጭሱ ደግሞ አይናችንን ያቃጥለን ጀመር፡፡ ዋሻችን በሴቶቹ ግጥም ብሎ ሞልቶአል፡፡ ሴቶች ፍርሃታቸው ከቁጥጥር ውጭና ከመጠን በላይ ነበር፡፡ የኛ ዋሻ ከሌሎች ይሻላል ብለው ሰላሰቡ ሁሉም ተገፋፍተው ነው የገቡት፡፡ በዚህ ሙቀትና መተፋፈግ መሀል እኔና ድሬሰሮቹ የሚመጡልንን ቁሰለኞች እናከም ነበር፡፡

ከብዙ ውይይት በኋላ ከቀኑ ወደ አስር ሰአት ሲሆን ደጃች አያሌው ራስ እምሩን በሌሊት ወደ ማለፊያ በሩ ሄደው ለማጥቃት ያሰቡትን ዕቅድ አስቀየሯቸው፡፡ ቀኑን ሙሉ ጠላት ያለበትን ቦታ አያጠናከረ ስለዋለ ማጥቃትና መውረር የማይቻል ነው፡፡ ስለዚህ ደጃች እያሌው የተሻለ ነው ብለው ያሰቡት ታክቲክ ጠላትን በማለፊያው እንዳይወጣ መዝጋት ነው፡፡ በዚህ መንገድ ከጀርባ የሚደርሰብን ጥቃትም ይቀራል ጠላት ያሰበውን እቅድም ማከሸፍ እንችላለን፡፡

ጨለማው እየገፋ ሲመጣ ፈጣን መልከተኛ መጥቶ ራስ እምሩ ከአምስት ሺ ሰዎች ጋራ በመሆን መንገድ መጀመራቸውን ነገረን፡፡ ወዲያውኑ ደጃች አያሌው ፀሀፊያቸውን ልከው የተሰማማነው ስምምነት ምን ደረጃ ደረሰ ብሎ እንዲጠይቅ አደረጉ፡፡ መልስ የተሠጠው በሚቁነጠነጥ ፈረስ ላይ በተቀመጠው በዮሐንስ ነበር፡፡ ስምምነት ኖረም አልኖረም ወደ ስለህለህ እየተጓዙ መሆናቸውን ተናገረ፡፡ ደጃች እያሌው ማድረግ የሚችሉት የተሻለ ነው የሚሉትን ነገር ነው፡፡ ተከትለው ለመሄድ ወይም ወደኋላ ለመቅረት ነፃ ነበሩ፡፡

ወዲያውኑ በቦታው የነበሩትን የጦር መኮንኖቻቸውን በሙሉ አስጠሩ፡፡ የጣልያኖችን ዕቅድ ጨምሮ ሁኔታውን ካብራሩ በኋላ እንዴት ማድረግ እንዳለብን ያለምንም ማወላወል ሀሳባቸውን እንዲሰጡ ጠየቁ፡፡ አብዛኛዎቹ



ባለንበት ቦታ እንድንቆይ ነው ድምፅ የሰጡት ግን ድንገት ራስ እምሩ ርዳታ ከፈለጉ ወይም ከጀርባቸው የሚጠቁ ከሆነ ለመርዳት ተዘጋጅተን እንጠብቅ የሚል ሀሳብ ነበር፡፡

ይህ ስብሰባ እየተካሄደ እያለ የጣልያን አውቶማቲክ መሣሪያዎች መንጣጣት ጀመሩ፡፡ የነጎድጓድ ድምፅ እያሰሙ እየደጋገሙ መድፎች ሲተኮሱ በጨረቃው ብርሃን የሚወረወር ብርሃን ያሳዩ ነበር፡፡ አልፎ አልፎ ጋብ ከማለት በስተቀር ሙሉ ማምሻውን በዚህ ሁኔታ ቀጠለ፡፡ ጣልያኖቹ ድንገተኛ ጥቃት እንዳይፈጠር ለመከላከል ያሰቡት ነገር ነበር፡፡ ምንም ኢላማ ወይ ግብ አልነበራቸውም ጥይቶቹ በዘፈቀደ በየቦታው ነበር የሚወድቁት፡፡

በጨረቃ ብርሀን ራታችን ለመብላት ተቀመጥን፡፡ ከፊት ለፊታችን ጥቂት ኪሎሜትሮች ርቀት ያለማቋረጥ የሚተኮሰውን የአውቶማቲክ መሳሪያ እና አልፎ አልፎም የመድፎቹን ተኩስ እናያለን፡፡ አዛዡ በዝምታ ቁጭ ብለዋል፡፡ ምግቡም ጣዕም አልሰጠም በደረቅ ጉሮሮ ላይ የሚወርድ ይመስላል፡፡ አልፎ አልፎ ብርድ ብርድ እያለኝ ሰውነቴን ያንቀጠቅጠኝ ነበር፡፡ የሚቀጥለው ቀን በእቅፉ ምን ይዞ ይመጣ ይሆን?

ትንሽ ጉርሻዎች ከጎረሰኩ በኋላ ደህና እደሩ ብዬ ወደ ድንኳኔ ሄድኩኝ፡፡ ድንኳኔ መረብ ያለበት ነበር ከዋሻ መግቢያ በኩል ካለ ዛፍ ስር ተወጥሮ ተዘጋጅቷል፡፡

ድፍን ያለ ፀጥታ በመላው ካምፕ ውስጥ ሰፍኗል፡፡ የሚነድ እሳትም አልነበረም፡፡ ሁሉም በወዲያኛው ወገን ባለው ትዕይንት ተመስጠዋል፡፡ በኋላ ያ ምሽት በጨረቃ ብርሃን ፊቴን ለመላጨትና ገላዬን ለመታጠብ ለምን እንደገፋፋኝ ይገርመኝ ነበር፡፡ በኔ በኩል ያለምንም ሀሳብ በድንገት ነበር ያደረግሁት፡፡ በዚህ ወቅትም የሚተኮሱ እውቶማቲክ መሳሪያዎችን አይነት ለመለየት ምን ያህል ርቀት ላይ እንዳሉ ለመገመት እየሞከርኩ ነበር፡፡

የታጠቡ ልብሶች ለብሼ በድንብ የተወለወለውን ጫማዬን አድርጌ ንፁህ ሆኜ ሰቆም ልገልፀው የማልችለው የደሰታ ስሜት ተሰማኝ፡፡ የማደርገው ነገር በሙሉ እስቤበት ሳይሆን ዝም ብየ ነበር የማደርገው፡፡ እሁን ደግሞ ሣጥኔ ውስጥ ያለውን ነገር አደራጀሁና ደጃች አያሌው በአደራ የሰጡኝን አሰር ሺ ሊሬ በኪሴ ያዝኩኝ፡፡ በንግድ የሰበሰብኩት የራሴ ሀያ ሺ ሊሬ ግን ሳጥኑ ውስጥ ተቀምጧል፡፡ ከዚያ በኋላ በሙሉ ሰውነቴ አልጋዬ ላይ ተጋደምኩና ራስ እምሩ ስላደረጉት ነገር ማሰብ ጀመርኩ፡፡

የሚያወራጭ አንቅልፍ ይዞኝ ነበር ማለት ነው የጥሩምባ ድምፅ ሰሰማ ነቃሁኝ፡፡ ሰአቱ ከሌሊቱ ስድሰት ከአሰር ነው የሚያሳየው፡፡ ወደ አዛዡ ሰጣደፍ ሄድኩ ልብሳቸውን ለብሰው በዘቦቻቸው ተከበዋል፡፡

"ምንድን ነው ነገሩ?"

"አትሰማም እንዴ?" አሉ ወደ ሰሜን አቅጣጫ እያመላከቱ

አሁን የጀሮ ታምቡር የሚበጥስ ድምፅ ተሰማኝ፡፡ መድፎቹና አውቶማቲክ መሳሪያዎቹ በነበራቸው አተኳኮስ ፍጥነት አልነበሩም፡፡ እርስ በራስ እየተፎካከሩ ተኩሱን ያቀልጡታል፡፡ ቆየሳ ተራራ በሶሰት ባውዛ መብረቶች ደምቆአል፡፡ ባሻጋሪ ግን ተወርዋሪ ኮከብ የሚመስሉ በአሳት በራሪዎች ይነዳል፡፡ ቦምቦች ከኛ ኪሎሜትሮች ርቀት በአፍ ጋጋ ማለፊያ ሲፈነዱ እንሰማለን፡፡

ጦሩን ለማሰባሰብ ጥሩምባው ያለ ማቋረጥ ይነፋ ነበር፡፡ ራስ አምሩ በሌሊት ማጥቃት ሰለጀመሩ ረዳት ጦር ይፈልጋሉ፡፡ አዚህ ሆነን ቆመን ማየት ወይም መጠበቅ አንችልም፡፡ ይቅርታ የማይድረግለት ከህደት ነው፡፡

ከግማሽ ሰአት በኋላ የሚበቃ ሰው ቁጥር ሰለተሰበሰበ መንገድ መጀመር ነበረብን ጓዝ ያገርዎች ግን ወደኋላ እንዲቀሩ ታዘዙ፡፡ በጨረቃ ብርሃን የሰዎችን ቁጥር መገመት አሰቸጋሪ ነበር፡፡ ነገር ግን አሁን የሚንቀሳቀሰው የጠቅላላው ጦር ቁጥር አራት ሺ አይሞላም፡፡ ሌሎቹ የት ቦታ እንዳሉ ለመናገር ቀላል ነገር አልነበረም፡፡

ከማለፊያ በሩ ምዕራብ በኩል ከተራራው ግርጌ ተጠለልን፡፡ ራስ አምሩም እዛው ቦታ ነው ያሉት፡፡ ቦታው የጣልያኖቹ ባውዛ መብራት ሰለበራበት የራስ አምሩ ሰዎች ለመንቀሳቀስ አልደፈሩም፡፡

ከአጭር ውይይት በኋላ የሁለቱ ጦር አዛገኖች አንድ ላይ ሆነው ለመዋጋት ተሰማሙ፡፡ ደጃች አያሌው የጥምር ጦሩን ሀላፊነት እንዲወሰዱ ተደረገ፡፡

ደጃዝማች አሁን በችሎታቸው ወይም በሙያቸው ላይ ነው ያሉት፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜም የራሳቸውን ሙሉ ሀይልና የመምራት ችሎታቸውን ሊያጠናከሩ ነው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜም ነፃ ሆኑ የሁሉም ነገር አሰተዳዳሪ እሳቸው መሆናቸው ተሰምቷቸዋል፡፡ በሚያሰገርም ፍጥነት የሁለቱን ጦር በየከፍሉ ከፋፍለው የሚደባለቀውን አደባልቀው አደራጁት፡፡ ሰንት ቦታ መመራት እንዳለበት የትኛው የጦር ክፍል ደግሞ የሚለማማው ቦታ የትኛው



እንደሆነ በትክክል አውቀውታል፡፡ ከዚህ በፊት የአካባቢውን ገበሬዎች ጠይቀው ሰለነበር የእያንዳንዱን ቦታ ጋራውን ወንዙን ሸለቆውን የአርሻ ቦታውን ሰም አቀማመጡን አውቀዋል፡፡ አያሌው ከሳምንታት በፊት አሰቀድመው ወሳኝ ጦርነት በዚህ ማለፊያ በር ላይ እንደሚደረግ ደርሰውበታል፡፡

ሁሉም ነገር ተደራጅቶ ሲያልቅ የተለያዩት የጦሩ ክፍሎች በጨለማው እየተሳቡ ወደፊት በመሄድ ቦታ ቦታቸውን ያዙ፡፡ ሁለቱ የጥንት መድፎች ጋራው ላይ በማለፊያው በቀኝ በኩል እንደማይታዩ ተደርገው ተጠምደዋል፡፡ ለመሸፈን መሞከሩ እንኳን ጥቅም የሌለው ድርጊት ነው ምክንያቱም ባሩዳቸው ሲጨስ ያሉበትን ቦታ ሰለሚያጋልጥ ነው፡፡

ሰአቱ ከንጋቱ አሰር ሰአት መሆኑን ያሳያል፡፡ የምሥራቁ አድማሰ ደግሞ ንጋት መምጣቱን ለማብሰር ፈጋ እያለ ነው፡፡

ያለንበት ቦታ እንደቆምን ቆየን የደጃዝማች አምሰት መቶ ዘቦችና የራሰ አምሩ ተመሳሳይ ቁጥር ዘቦች በዙሪያችን አሉ፡፡ ሁለቱም የጦር አዛገኖች ለረዥም ጊዜ በዝምታ ቆመው ነበር፡፡ አያሌው ቀና ብለው "የለም አሁን በዚህ በጋራው አካባቢ የሚገኝ ዋሻ መፈለግ አለብን" አሉ፡፡

ይህንንም ቢሆን አሰቀድመው አሰበውበትና አቅደውት ነበር

ያለምንም ችግር ዋሻውን አገኙ ግን መጠኑ ትንሽ ሆነ፡፡ ቢበዛ ሀያ ሰዎች ብቻ ነው ሊያሰጠልል የሚችለው ሰለዚህ ወታደሮቹ ተበታትነው ከዛፎች ስር ወይም ከድንጋዮች ጀርባ መጠለያ እንዲፈልጉ ታዘዙ፡፡

የዋሻው መግቢያ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ነበር፡፡ ፈልገን የምሥራቁን አቅጣጫ አገኘን፡፡ ቦታው የጋራው እናት ላይ ሆኖ በትልልቅ ድንጋዮች የተከበበ ነበር፡፡ ከዚህ ሆኖ አንድ ሰው ሳይታይ ሰለህለህን ማየት ይችላል፡፡

ከጋራው ወደታች ግማሽ ኪሎሜትር ሰፋት ያለው ሜዳ አለ፡፡ ትንሽ ወንዝ በዘምባባ ዛፎች ተሸፍኖ ከሜዳው በሰተቀኝ በኩል ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ይወርድና ከሌላ ከሰሜን ምሥራቅ ከሚመጣ ወንዝ ጋር ይገናኛል፡፡ በቀጥታ ከፊት ለፊታችን የአቃቢ ሰአት የአዲ ሀይማነል እና የሰለህለህ ጋራዎች ወደ ላይ ቆመዋል፡፡ የሰለህለህ ጋራ የአፍ ጋጋ ማለፊያን አልፎ በግራ በኩል እኛ ካለንበት ዝቅ ብሎ ነው የሚገኘው፡፡

ብርሃን እየጨመረ ሲሄድ ጣልያኖች ያሉበትን ቦታ ማየት እንችል ነበር፡፡ የተቆፈሩ ጉድቦች መከለያ ግንቦች የጋራው ወገብ ላይ በተራ ተሰርተውና



የሰለክለካ ግንባር ከጣሊያኖች በኩል የተነሳ ፎቶግራፍ በሚገርም ሁኔታ ፀሃፊው እንደገለፁት የጭነት መኪኖች አቧራ ማስነሳትና ስለ ታንኮች አሰላለፍ በትክክል ያሳያል (በሰባስቲያን ኦኬሊ Sebastian O'Kelly) መልካም ፈቃድ



ተዘጋጅተዋል:: ሰላሳ ታንኮች ወደኛ ዞረው ዝቅ ብለው የሚዳው ጫፍ ላይ ቆመዋል::

ተኩሱ ለረዥም ጊዜ ቆሞ ስለነበር የሚሰማ ድምፅ አልነበረም:: በዚያች ውብ የንጋት ሰአት ላይ ሁሉም ነገር ሰላም ይተነፍስ ነበር:: ማዕበል ከመምጣቱ በፊት እንደሚሰፍነው ፀጥታ ነው:: ፀሐይ ከመውጣቷ በፊት ማለቂያ የሌለው የሚመስል የጭነት መኪኖች ሰልፍ ከአከሱም በኩል እያጉረመረመና የአቧራ ጉም እያቦነነ ሲመጣ አየን:: መኪኖቹ ጉድቦቹ የተቆፈሩበት ቦታ ሲደርሱ ያቆሙና ወታደሮችን ያለማቋረጥ ያራግፉ ነበር:: ሥርአት ያለው አደረጃጀት ነበር:: የጭነት መኪኖቹ እንደአመጣጣቸው ወዲያው ተመልሰው ይሄዳሉ:: ወታደሮቹ ይሰበሰቡና በሥርአት በሰልፍ እየሆኑ ወደ ምድብ ቦታቸው ይሄዳሉ:: አልፎ አልፎ ጩኸት ይሰማል:: ሁሉም ነገር እንደ ሞተር መኪና ነው የሆነው ያለምንም ውዥንብር በፍጥነት ነበር የሚካሄደው::

ደጃዝማች ተመስጠዋል:: የጠላትን እንቅስቃሴ ትንፋሻቸው የሚቆም እስከሚመስል ድረስ በከፍተኛ ትኩረት ሲከታተሉ ነበር:: ፊታቸውን ሳያዞሩ እጄን ይዘው እስከሚያመኝ ድረስ ጨበጡኝ:: እዎ እኔም በሚገባ ተረድቻቸዋለሁ:: በተፈጥሮአቸው የጦር አዛዥ የሆኑ እኚህ ሰው በቅናት ይንገበገቡ ነበር:: እንደዚህ አይነት የተደራጀ ጦር የመምራት አጋጣሚ አልነበራቸውም:: ቢሆንማ ኖሮ ለንጉሡም ሆነ ለእባት አገራቸው ችሎታቸውን ያሳዩ ነበር:: በተቃራኒው ያልተደራጁና ያልሠለጠኑ ሰዎችን መምራት ነበረባቸው:: እነዚህ ወታደሮች ደግሞ አግራቸው ላይ እንደ ጭነት ነበሩ:: ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ትልቁ ሸክም አገሩን ከድቷል ተብለው መጠርጠራቸው ነው::

በመሀሉ ጣልያኖቹ በዘምባባ ዛፎች ውስጥ በወንዙ አካባቢ የኛ ግንባር ጦር ተደብቆ ባለበት ቦታ እንቅስቃሴ ያዩ ይመስላሉ:: ሁሉም ታንኮች አውቶማቲክ መሳሪያቸውን መተኮስ ጀመሩ:: ወደ አርባ የሚሆን ፈጣን አሩምታ ተኩስ እኛ ወዳለንበት ጋራ ዳገት ላይ ተኮሱ::

ማዕበሉ ጀመረ:: ገና ቃል ሳንተነፍስ ከኛ መጠለያ ፊት ለፊት ብዛት ያለው ፍንዳታ ጀመረ:: የሚያስነሳው ጠጠርና አቧራም እንደዝናብ ላያችን ላይ ይወርድ ጀመር::

ቡም! ቡም! ከኛ መድፎች የመጣ ድምፅ ነበር:: ሁለቱ በደንብ የተነጣጠሩ ተኩሶች ስለነበሩ እያንዳንዳቸው ታንክ ሰባበሩ:: ቀጥሎም ፈጠን ያለ አፀፋ እጠገብ በነበሩ አስር ቦታዎች ተሰማ::



ከመጀመሪያው የጦር ሜዳ ፎቶ የሚቀጥል ነው፡፡ የጣልያን ታንኮችና ወታደሮች ወገን ላይ ጥቃት ሲያደርሱ፤ አጉልቶ ከታየ ደግሞ ሜዳው ላይ የወደቁ የኢትዮጵያውያን ተዋጊዎች አስከሬኖች ይታያሉ፡፡ ፎቶግራፉ በሴባሰትያን ኦኬሊ (Sebastian O'Kelly) መልካም ፈቃድ



በሚያስፈራ ጩኸት በመቶዎች የሚቆጠሩ የፈታውራሪ ተሻገር ሰዎች አዲስ በተከፈተላቸው በታንኮች መሀል ባለ ከፍተት እየሾለኩ ወደ ሜዳው መገስገስ ጀመሩ፡፡ የመጀመሪያውን የጣልያን ወታደሮችን የቀበሮ ጉድጓድ ደርመሰው ወደ ሚቀጥለው ጥቃቱን ቀጠሉ፡፡ እዚህ ቦታ ሲደርሱ ግን ለመጀመሪያ ጊዜ ከእጅ በምብ ጋራ ትውውቅ ጀመሩ፡፡ አይናቸው ላይ አንድ ነገር እንደ ቀይ ብልጭታ ሲበራ እዩ ጆሮም የሚያደነቁር ነበር፡፡ ጥቂት ጓዶቻቸው ወደ ላይ ወደ ሰማይ ተወርውረው ሆዳቸው ተበትኖ ወደ መሬት ይዘረገፉ ነበር፡፡ አይ! ይህ የሰይጣን ሥራ መሆን አለበት፡፡ በሰው እጅ የተሠራ ነገር ሊሆን አይችልም፡፡ ታዲያ ማነው ይሄን የሚቋቋመው?

የጠላት ጥይትና መድፍ ከኋላቸው እየተከተላቸው በፍርሀት ወደኋላ አፈገፈጉ፤ ቁጥራቸው በግማሽ ተቀንሶ ተመልሰው የመጀመሪያ ቦታቸው ወደ ነበረው ጫካ ገቡ፡፡

ውጊያው አሁን በመላው ግንባር በኩል መካሄድ ጀምሮአል፡፡ ወደ አስር ሺ ከሚሆኑት ጠመንጃዎች የሚመጣው የተኩስ ድምፅ በተመሳሳይ ፍጥነት የማያቋርጥ ጉርምርምታ ያሰማ ነበር፡፡ ጩኸት እና የጥይት አርሳሶች ፉጨት ከጠላት በሚተኮሱ ከባድ መሳሪያ ፍንዳታዎች ድምፅ እየሩን ሞላው፡፡ በአያንዳንዱ ወደ እኛ አቅጣጫ በሚመጣው ከባድ መሳሪያ አርሳሰና ፍንጣሪ በደመ ነብስ ከመቅፅበት መሬት ላይ እወድቅና እንደገና ደግሞ ዘልዬ አቆማለሁ፡፡ አስቃቂ ድራማው የሚሰብ ነገር ስላለው ከማየት አልተቆጠብኩም፡፡ ከወንዙ ማዶ ባለው ሜዳ ላይ አንድ በአንድ እያለ የከባድ መሳሪያ ጥይት ይወርድና እየፈነዳ ትልቅ ጉድጓድ ይምስ ነበር፡፡ አሁንም አሁንም ከአፈርና ከድንጋይ ፍንጣሪዎች ጋር ሰው ወደላይ ሲጎና አያለሁ፡፡ ብዙ በቅሎዎች የታሰሩበትን በጥሰው ያለ ከርቻ ወዲያና ወዲህ ሲጋልቡ ነበር፡፡

ብርርርርር! አሃ! ነፍስ አጥፊ ወፎች እንደገና እየመጡ ነው፡፡ ወደ ዋሻችን እየዳህን ገባን፡፡ ወዲያውኑ አውሮፕላኖቹ በእናታችን ላይ እያንዣበቡ በአፍ ጋጋ በር ላይና በሜዳው ላይ በምብ ይጥሉ ጀመር፡፡ የኛ መድፎች ያሉበት ቦታም ታውቋል፡፡ በእርግጥ ይመታሉ ነገር ግን እስከአሁን ድረስ ያስመስለስ ኢላማቸውን እየመቱ ነበር፡፡ በመሀሉ አውሮፕላኖቹ እኛን ትተው የጓዝና ስንቅ ከፍላችን መደብደብ ጀመሩ፡፡ እንደዚያ ሲሆን ወጥተን ተመለከትን ነገር ግን ተመልሰው ሲመጡ ወደ ዋሻችን እየዳህን ለመመለስ ዝግጁ ነበርን፡፡

ፀሀይ በዝግታ ወደላይ እየወጣች ነበር። ከጥዋቱ ሶስት ሰአት ሲሆን የኛ መድፎች በተርታ የተሰለፉንትን ታንኮች ወደ ምዕራብ እንዲያፈገፍጉ አስገደደጿቸው። የመሀል ጦራችን ጠላትን ከመሀል ጋራው እንዲሸሽ አድርጎታል ሆኖም ተደራቢ ረዳት ጦራቸው ተጨምሮ ከአንድ ሰአት ሀይለኛ ውጊያ በኋላ መልቀቅ ነበረብን ነገር ግን እስከጋራው ግርጌ ድረስ ብቻ ነበር። በግራ በኩል ያለው የጎጃም ጦር ደግሞ ጠላትን ብዙ መቶ ሜትሮች እንዲያፈግፈግ አለደርጎ ቦታውን ተቆጣጥሮ መከቶ ይዟል። ጠላት ብዙ ወታደሮች ማምጣት ጀምሮ ስለነበር ተጨማሪ ሀይልም ይፈለግ ነበር ። ተጨማሪ ሀይል ከየት ይመጣል? ዳገቱን የያዘው የደጀን ጦራችን ሜዳው ተኩሰ በተኩስ ስለሆነ ለቆ መውጣት አልቻለም። ሞከረው ነበር ነገር ግን በየጊዜው ወደኋላ መመለስ ነበረባቸው።

ከቀኑ አምስት ሰአት ሲሆን ጣልያኖቹ ውጊያውን ወደ ምዕራብ በኩል ወደተራራው ግርጌ ለመግፋት ሲሞከሩ አስተዋልኩኝ። አቅዳቸውን ለመረዳት ቀላል ነበር። ከሰአት በኋላ ሲሆን ማለፊያውን ዘግተው መሸሽ እንዳንችል ለማድረግ ነው። ከዚያ ደግሞ ዙርያውን የከበበው ጦር ከምዕራብ አቅጣጫ መጥቶ ሌሎችን እንዲቀላቀል ነው።

ምንም ያህል ጉዳት ይድረስ ፊታውራሪ ዘውዱ ጎጃሞችን እንዲረዱ ታዘዙ። ከሁለት ሺ ሰዎች ጋር በመሆን እየጋለቡ ቁልቁል ወደ ሜዳው ወረዱ። ያለ ምንም ፍራቻ በተኩሱ መሀል ወደ ፊት ገሰገሱ ማዶ ሲሻገሩ ግን ግማሽ ሰዎቻቸው አልቀዋል። ብዙዎቹ ሞተዋል ሌሎቹም ወደኋላ ተመልሰዋል። ዘውዱ ሲጋልቡት የነበረው በቅሎ በጥይት ጭንቅላቱን ተመቶ ወዲያው ሞተ።

ዘውዱ በሚያጠቁበት ወቅት ደግሞ የራስ እምሩ ጠባቂ ጦር የጠላትን የምዕራብ ጎን እንዲያጠቃ ታዘዘ። የራስ እምሩ ጠባቂዎች የንጉሡ የክብር ዘበኛ አባሎች ናቸው በአዲስ አበባ ዘመናዊ የአውሮፓ ወታደራዊ ሥልጠና የተሰጣቸው ነበሩ። ወታደሮቹ በተማሩት መሰረት ምሰጋና በሚገባው ሁኔታ መዋጋት ጀመሩ። የቦታውን አቀማመጥ በመጠቀም የጣልያኖችን ሬጅምንት ማጥቃት ጀመሩ። በመጀመሪያው ድንጋጤ ጠላት የነበረበትን የመጀመሪያውን ጉድብ ሲለቅ ጠቅላላ ለቆ የሚሄድ መሰሎ ነበር።

ከቀኑ ሰድስት ለአት ሲሆን ከዋሻችን መግቢያ ቁጭ ብለን ምግብ ቢጤ ለመቅመስ እየሞከርን ነበር። ምን መሆኑን አስከምንለይ ድረስ ያለምንም



ማስጠንቀቂያ ለላይ አውሮፕላን እንደ ጭልፊት ቁልቁል ወደኛ ተወረወረ። ከንፎቹ ለጥቂት እለቱን ነከተውት ነበር። አውሮፕላኑ ተመልሶ ሲመጣ ገና ወደ ዋሻው ተመልሰን እየገባን ነበር በዚህ ጊዜ ግን አውቶማቲክ መሳሪያ እየተኮለብን ነበር። ብዙ ጥይቶች እየነጠሩ የዋሻውን ጣሪያ መቱት። አውሮፕላኑም ተመልሶ አልመጣም ግን ተገኘን እነሱም እዛ ዋሻ ውስጥ ማን እንደተደበቀ አውቀዋል።

ብዙም አልቆየም ምናልባትም አንድ ለአት ተኩል ይሆናል አያፏጨ ቦምብ ሲወርድ መሬቱ እንደምድር መንቀጠቀጥ ይርድ ነበር። በጥንቃቄ ወደ ውጭ ተለመለከትኩ። ከኛ ሀያ ሜትር ርቀት የነበረ ዛፍ በቁሙ ተሠንጥቋል። ከስሩ ግን ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የሚተነፍስ ለው የነበረ ወድቋል። ከጭንቅላቱ አገጩ ብቻ ነው ጥርስ እልባ ሆኖ አንገቱ ላይ ተንጠልጥሎ የሚታየው። የግራ እጅና የግራ እግሩ እስከ ጭኑ ድረስ የሉም። በግራ ጎን ደረቱ ተከፍቶ እንጀቱ ይታያል። የጎራዴው ግማሽ እንኳን ሳየቀር የለም።

ማን እንደነበረ አውቄአለሁ። ከአጭር ጊዜ በፊት በፈገግታ ተለያይተናል። እሱም ልጅ ይሻል ነበር ከእድዋ የነጋዴ ልጅ ነው። ከልጅነት ጓደኞቼ አንዱ ሲሆን የደጃች አያሌው ጦር ውስጥ ተሰልፎ እያገለገለ ነበር።

አውሮፕላኖቹ ግን ለትዝታ ጊዜ የሚሰጡ አልነበሩም። እንደ መጥፎ የዝናብ ነጎድጓድ እያጓሩብን የሚወረወር የእሳት ነበልባል በአይናችን እያየን መሬቱም እየተንቀጠቀጠ ጥቅጥቅ ባለ አቧራ ጉም ታፈን። የነበረንን የጋዝ ጭምብል አድርገን ነበር ግን መልሰን ማውለቅ ነበረብን። በጣም ይሞቅም ነበር። እንደገናም የጭምብሎቹ አየር መዘዋወሪያዎች በአቧራ ተደፍነው ነበር።

መቼ እንዳቆመም አላውቅም ለብዙ ደቂቃዎች ፋታ አግኝተን ነበር እንደገና ተመሳሳይ አስፈሪ ድብደባ ሲጀመር። ድብደባው በዋሻው ጣራ ላይና በጀርባው በኩል ነበር አውሮፕላኖቹ እንደገና ቦምብ ለመጫን ሲመለሱ መድፈኛው እንዲደበድብን ታዞ ነበር። የነበርንበትን ቦታ አውቀዋል። ቶሎ ቶሎ አሁንም አሁንም ቦምብ ሲወርድብን ጠቅላላው ዋሻ ይንቀጠቀጣል እኔም እለቱ የተሠነጠቀ መሰሎኝ ነበር። እለቱ ችሎ ይቋቋመው ይሆን? ወይስ ተደርምሶ ይቀብረን ይሆን? አሰቃቂ ሰሜት ነበር!

ነገር ግን ያ ብቻ አልነበረም። ጠላት ጣራው ላይ መድፍ ይተኩስ ጀመር አርላሶችም መግቢያው ላይ ይፈነዱ ጀመር መውጫውን ለመዝጋት ነው ሀሳባቸው።

ያን ቀን ዋሻውም ሆነ እኛ ራሳችን ያን ሁሉ ነገር እንዴት እንደቻልነው አይገባኝም፡፡ ድምፁን በደንብ አልሰማም ነበር ከባድ ራስ ምታትም ተከትሎ መጣ፡፡ በቦምብ ውርጅብኙ የተናወጠው እንጎላችን በደንብ መሥራት ያቆመ ይመስላል ምናልባትም ለዚያ ይሆናል ከእብደት የተረፍነው፡፡ እኔም ምንም አይነት ስሜት በጭራሽ አልነበረኝም ኩርምትምት ብዬ ያለምንም መንቀሳቀስ ቁጭ አልኩኝ፡፡ እንደፈለገው ይሁን፡፡ ከዚህ የባሰ አይመጣም፡፡ ሞት አረፍት ነው ብዬ አሰብኩ፡፡ ሁላችንም ብንሆን ሞትን የተመኘን መሰለኝ፡፡

ራስ አምሩ እግራቸውን አጣምረው አገጫቸውን በእጃቻቸው ደግፈው ጎላ ያሉ አይኖቻቸው አንድ ቦታ ተተከለው ቁጭ ብለዋል፡፡ ፈገግም ያሉ ይመስላል፡፡ ጨለማና ጭንቅ ያለ ነገር ቢሆንም እርጋታ ነበር፡፡ አልፎ አልፎ አግር አቀማመጣቸውን እየቀየሩ ድምፅም ያሰሙ ነበር፡፡ የሚያሰቡትን ነገር ለማወቅ አስቸጋሪ ነበር፡፡ ምናልባትም የዮሐንስን ምክር መሰማታቸው ፀፀቷቸው ይሆናል፡፡ ሁላችንም አየመሩ ወጥመድ ውስጥ እንዳስገቡን እያሰቡ ይሆን?

ደጃች አያሌው ጠንካራ ከሆነው ከወገብ በላይ ሰውነታቸው ጋር በሃሳብ ተውጠው ተቀምጠዋል፡፡ የውጊያውን ሁኔታ መረጃ ለመስማት እየጠበቁ ያለትግሰት ጣቶቻቸውን እያጠፉ ይዘረጉ ነበር፡፡ ረዳቶቻቸው ሳይታከቱ እየሾለኩ ይመጡና ዜና ያቀርባሉ ጥያቄም ይጠየቃሉ አንደገና ደግሞ ከደጃዝማቹ አዲስ ትዛዝ ይቀበላሉ፡፡ ምንም እንኳን ራሳቸው ማየት ባይችሉም የመላው ጦሩን እንቅስቃሴ የት አንዳለ ርዳታ ይፈልጉ እንደሆን መረጃ ያገኛሉ፡፡ እኔ እንደማስበው ከሆነ ራሳቸውን እንዳመማቸው ቢናገሩም ከመሀከላችን አሳቸው ብቻ ነበሩ ከማሰብ ችሎታቸው ጋር የነበሩ፡፡

የንስሐ አባትየውና ሁለት የጦር አዛገሮች ደግሞ አጠገቤ ተቀምጠው ሲፀልዩ ይሰሙ ነበር፡፡ ከሁሉም ቅዱሳኖች ቅዱስ ጊዮርጊስ ነበር በብዛት የሚጠራው፡፡ *ቅዱስ ጊዮርጊስ የአቢሲኒያ የጦር ጠባቂ ነው፡፡ በ1888 እመተ ምህረት በሱ ቀን ነበር የአድዋ ጦርነት የተካሄደው አናም በሱ አርዳታ በውጊያው ድል ተገኝቷል፡፡ አሁን ደግሞ ያንን ቀን በማሰታወስ ቅዱሰ ጊዮርጊስ እየተነሳ ነው፡፡ በፀሎት አሁን በተከታዮቹ ጎን እንዲቆም ጥሎ አንዳይጥላቸው እየተጠየቀ ነበር፡፡

---

** የቅዱስ ጊዮርጊስ ምስል የተጠለፈበት ጨርቅ እንደ ጦር አርማ ይወሰድ እንደነበርና በ1927 አም መሐል ሠፋሪ ተብሎ ለሚጠራው ጦር በስጦታ መልክ እንደተሠጠ ተዘግቧል፡፡ ይህንን የሚሳይ ፎቶግራፍ በመፅሐፍ ይገኛል*

*1935 Invasion of Abysinia, David Nicole*



ከቀኑ አሰር ሰአት ሲሆን አልፎ አልፎ ከተናጠል አውሮፕላኖች ከሚጣለው ቦምብ ፍንዳታ ድምፅ በስተቀር ከዋሻው ድብደባ ለአንድ ሰአት የሚሆን ፋታ አግኝተን ነበር ፡፡ እሁን ጠላት በግራ በኩል በብዙ ወታደሮች አያጠናከረ ከመሆኑ በስተቀር አሰላለፉ ያው እኩለ ቀን ላይ እንደነበረው ሆኖ አናያለን፡፡ ከፍተኛ ግፊት ቢኖርም የራስ አምሩ ጠባቂዎች ተቋቁመው ነበር ነገር ግን ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ስለሞቱ በቅርቡ የመጨረሻ ሀይላቸው እንደሚሟጠጥ ነው ስለዚህ የደጃማች አያሌው ጠባቂዎች ለርዳታ መላከ ነበረባቸው፡፡

የኛ መሀል ጦር ደግሞ ወደ ምዕራብ በኩል ተንቀሳቅሶ ከግራ ከንፍ ካለው ጦር ጋራ ጎን ለጎን ሆኖ እየተዋጋ ነው፡፡ እንደ መረጃው ከሆነ ሁሉም ወታደሮች የሚያኮራ ጀግንነት አሳይተዋል፡፡

የጠላት የቀበሮ ጉድጓዶች በተያዙበት ጊዜ ብዛት ያለው ንብረት እንደ ጠመንጃ፣ አውቶማቲከ መሳሪያና ጥይቶች ተማርከው ነበር፡፡ ችግሩ በአጅ ቦምቦቹ ምክንያት ሰዎቹ ቦታ ለመልቀቅ ይገደዱ ነበር፡፡ የአጅ ቦምቦችም ቢሆን በብዛት ተማርከው ስለነበር መልሰው ወደ ጠላት ይወረወሩ ነበር፡፡ በርግጥ የሠይጣን ሥራ ናቸው ምክንያቱም የሚፈነዱት ጣልያኖቹ ሲወረውሯቸው ብቻ ነበር፡፡ ከመወርወሩ በፊት ቀለበቱን መመንጨቅ እንዳለባቸው አቢሲኒያውኖቹ ገና አልደረሱበትም ነበር፡፡

በወንዙ በኩል የነበሩ ሰዎች ከሚታመን መጥን በላይ እንደሞቱም ተነገረን፡፡ እኔም ወደ ጫካው ዞር ብዬ ከተመለከትኩ በኋላ ብዙ ሰው ስለመሞቱ ምንም ጥርጣሬ አልነበረኝም፡፡ ያን ቀን ጠዋት ለምለምና አረንጓዴ የነበረው ጫካ የተሰባበሩ ግንዶች ብቻ ቀርተውበት ይታያል፡፡

በአሥራ እንድ ሰአት እየዳህን መውጣት ነበረብን፡፡ እሰቃቂው ድብደባ እንደገና ጀምሮአል፡፡ በአሥራ ሁለት ሰአት በቀኝ ከንፍ ያለው የኛ ጦር ረጅም ጊዜ መከቶ መቆየት እንደማይችል የሚገልፅ መልክት ደረሰን፡፡ ጣልያኖቹ ከነበራቸው ሀይል በእሰር አጥፍ ጨምረው አያጠቁ ነው፡፡ ደጃዝማች አንዳሉት እሁን መውጫ መግቢያውን ሊዘጉት ነው፡፡

ለርዳታ የሚላከ የደጅን ጦር የለም ስለዚህ በመሀል የተሰለፉት ፈታውራሪ ዘውዱና ሙላው ቦታቸውን ለቀው የቀኝ ከንፉን እንዲያግዙ ታዘዙ፡፡ ወደኋላ ለማፈግፈግ አንዲረዳ እስኪጨልም ድረሰ መከቶ መያዝ አስፈላጊ ነበር፡፡ ዙርያውን ከበባ ለማድረግ የሞከረው የጣልያን ጦር ወሬ የለም፡፡ የት ቦታ

እንደሆኑም ማንም አያውቅም፡፡ ፊትለፊት እናገኛቸው ይሆን? ወይስ ከነሱ መራቅ እንችላለን? አውሮፕላኖች እንደ ጉድ በአየር ላይ እያንዣባቡ ባሉበት ሰአት ወጥቶ ለመሄድ መሞከር የማይታሰብ ነው፡፡ ጨለማ እስኪገባ የቀኝ ከንፉ ያለበትን ቦታ ተከላከሎ ይጠብቅ ይሆን?



በራስ ካሳ ግንባር የእጅ ቦምብ ሲወረወር በጣልያኖች የተሣለ (ምስጋና ፋሲል ጊዮርጊስ)

እንደኔ ከሆነ ያን ቀን ፀሀይዋ እንደዚህ ተዝናንታ ዝግ ብላ ወርዳ አታውቅም፡፡ ሌላ ጊዜ አጭር የነበረው የቀን ብርሃን ለዕድሜ ልክ ረዥም መሰለ፡፡ አውሮፕላኖችም ቢሆን ሲመሽ ጨለማው ሳይገባ ወደ ቤታቸው መሄድ ያለባቸው መሆኑን የዘነጉት ይመስላሉ፡፡



ቢሆንም ሁለም ቀን ማቆሚያ እንዳለው ሁሉ ይህ ቀንም አቆመ፡፡ ወደኋላ የማፈግፈግ ትዛዝ ሲሰጥ ገና መጨለም አልጀመረም፡፡ መድፎቹ ከሌላ ጊዜ በላይ እንደነጎድጓድ ይጮሃሉ፡፡ የጣልያን ባውዛ መብራቶችም ሥራቸውን ጀምረዋል፡፡ ያ ሁሉ መድፍ እየተተኮሰ ከዋሻው ሾልከን ወጣን ጋራውን ቁልቁል ወርደን ሜዳው ላይ ወደሚጠብቁን ፈረሶቻችን ሄድን፡፡ ቃኝ ጦር ፊት ለፊት ተልኮ ስለነበር እነሱን መከተል ጀመርን፡፡

ጨረቃዋ ጥርት ባለው ሰማይ ላይ ታበራለች፤ ሁሉም ነገር ሰላም የሚያበስር ይመስላል፤ እኛም ግልቢያችን ቀጠልን፡፡ ከኋላችን የሚጮኸው የመድፍ ድምፅ ብቻ የቀኑን ውሎ ያስታውሰን ነበር፡፡

ወዲያውኑ ወታደሮች እየሮጡ እኛን ማለፍ ጀመሩ፡፡ ማንም ሰው ሲያስቆማቸው አይችልም ነበር፡፡ ሁሉም ወደ ማረፊያ ቦታቸው ነበር የሚሮጡት፡፡ ቀን መከተው በመዋላቸው ረከተዋል ደግሞም ደከመዋል፡፡

ከምሽቱ አንድ ሰአት ተኩል ሲሆን ትልቅ ዋሻ ያለበት ቦታ ደረስን፡፡ ተቀመጥን ግን በሀሳብ ተውጠናል፡፡ በየቦታው ጩኸትና ትዛዝ ነው የሚሰማው፡፡ "ጫን!" የማፈግፈጉ ትዛዝ ጭንቀት ፈጥሯል፡፡ ሁሉም የሚሮጠው የሚይዘውን ይዞ ወደ ቤቱ ለመሄድ ነው፡፡ ለነሱ ጦርነቱ አብቅቷል፡፡ ሙሉ ቀን በዋለው ውጊያ ጠላት አላፈገፈገም እና ባለድል የሆነ ይመስላል፡፡ በሚመጡት ቀናት ከእንደዚህ አይነት አስደንጋጭና አስከፊ ሁኔታ ለማምለጥ ወታደሮቹ ከማድረግ የሚቆጠቡት ነገር የለም፡፡ ወደ ደቡብ የሚጎርፈወን ሰው ለማስቆም የተደረገ ሙከራ ሁሉ አልሰራም፡፡ መንገደኛውን ለመመለስ የተላኩ ወታደሮች ችግር ላይ ወደቁ እንዲያውም ሁለቱ በጥይተ ተመተው ወደቁ፡፡ በብዛት ለሚጎርፈው ሰው መንገድ መልቀቅ ነበረባቸው፡፡

ሴቶቹ የባሱ ነበሩ፡፡ "ሩብላ" የሚባል ነገርና "ጥልያን" የሚባል ነገር የሚበቃቸውን አይተዋል፡፡ ለነሱ በረሀ ሲጓዝ ውሃ ያለበት ቦታ እንደሚጠራው መንገደኛ ቤታቸው ጠርቷቸዋል ፡፡

ሁለቱ የጦር አዛዦች አማራጭ አልነበራቸውም፡፡ ወታደሮቻቸውን ካልተከተሉ ሁለት ሰአታት በማይሞላ ጊዜ አስር ከማይሞሉ ታማኝ አሽከሮቻቸው ጋራ ብቻቸውን ወደኋላ እንደሚቀሩ ነው፡፡

ያን ቀን ማምሻውን ደጃዝማች አያሌው (ራስ እምሩም ሳይደርሳቸው አይቀርም) ከንጉሡ የተላከ ደብዳቤ ይደርሳቸዋል፡፡ በደብዳቤውም ጣልያኖች በሚቀጥሉት ቀናት ትልቅና መጠነ ሰፋት ያለው ጥቃት ለማድረግ እያሰቡ

መሆኑን ይገልፃል፡፡ አያሌው ያሰቡት እንዲህ አይነቱን ጥቃት ለመቋቋም አስቸጋሪ ስለሆነ የሰው ሕይወት በከንቱ ከሚጠፋ ወደኋላ ወደ ተከዜ ወንዝ እንመለስ ነበር፡፡ ደብዳቤው ደግሞ የተፃፈው ከአንድ ሳምንት በፊት በደሴ ከተማ ስለነበር ጉዳዩ ግልፅ ሆነ፡፡

በየካቲት ሀያ ሶስት በሰለህለህ በተካሄደው ውጊያ አቢሲኒያኖች ተሸንፈዋል ወይ? የዚህ ጥያቄ መልስ ሁለት ነው፡፡ ሽንፈት ነውም አየደለምም ነው፡፡ እስኪጨልም ድረስ ጣልያኖቹ መግፋትና አዲስ ቦታ መያዝ አልቻሉም ነበር፡፡ ስለዚህ ዕቅዳቸውን አላሟሉም ነበር ምንም እንኳን የመሳሪያ ጥራትና የአደረጃጀት ልዩነትን ሳይጨምር በቁጥር ከአቢሲኒያውያን ቢበልጡም፡፡ የደጃዝማች አያሌውና የራስ እምሩ ጦር ተጣምሮ ከአስር ሺ አይበልጥም ነበር፡፡ የተረፈው ጦር ወይም ሸሽቷል አለበለዚያም በአውሮፕላን ድብደባ ምክንያት በውጊያው ሳይደባለቅ ቀርቷል፡፡ እነዚህን ያልተደባለቁትን በጠዋት ማሰባሰብ ቢቻል ኖሮ ጣልያኖቹ እስከ ሃያ ሺ የሚደርስ ወታደር ይጋረጣቸው ነበር፡፡

ነገር ግን አቢሲኒያኖች ደግሞ የመድፉን፤ አውቶማቲክ መሳሪያውን፤ የእጅ ቦምቡን ከሁሉም በላይ የአየር ድብደባውን ተቋቁመው ለሁለት ሶስት ቀን መቆየት ይችሉ ነበር? በፍፁም የማይቻል ነገር ነው፡፡ የእጅ ቦምቦች "የሙሶሎኒ ወንበዴዎች" ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡ እናም በአቢሲኒያውያን ላይ ትልቅ ሽብር ነበር የፈጠሩት፡፡ በዛው ልክ ደግሞ የነሱ ጎራዴ ጣልያኖቹ ላይ ተመሳሳይ ሽብር ይፈጥር ነበረ፡፡ በተጨማሪም ወታደሮቹ የነበራቸው የውጊያ ፍላጎት የተዳከመ ነበር፡፡ ምክንያቱም ለአንድ ወር ያለምንም ነገር ዝም ብለው መቀመጣቸውና፤ በተከታታይ ከሚደረገው የአየር ድብደባ ተጨማሪም ጣልያኖቹ በአውሮፕላን በሚበትኑት ፕሮፖጋንዳ ወረቀቶች ጭምር ነው፡፡

በኛ በኩል የደረሰውን ጉዳት ለመናገር አስቸጋሪ ነበር፡፡ የሞቱና የቆሰሉ ቁጥር ሶስት ሺ ሲደርሰ ይችላል፡፡ በጣም የተጎዳው ደግሞ የራስ እምሩ ጠባቂ ክፍል ነው ከአምስት መቶ ወሰጥ ከሁለት መቶ በላይ የሆኑ ብቻ ነበር የተረፉት፡፡

በጣልያኖቹ በኩል የደረሰው ጉዳት ደግሞ በራሳቸው ዘገባ መሰረት ዘጠኝ መኮንኖች፤ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ነጭ ወታደሮችና ሁለት መቶ ሃምሳ አስካሪሶች ነበረ፡፡ የቆሰሉትን ቁጥር ማግኘት አልቻልኩም ቢያንሰ ቢያንሰ ወደ አንድ ሺ ይጠጋ ነበር፡፡



በየካቲት ሃያ ሁለትና ሀያ ሶስት በተደረገው ጥቃት ሰለ ጣልያኖች ቁጥር ከጣልያኖች ያገኘሁት መረጃ በቀላሉ ይህን ይመስል ነበር፡፡ ጦሩ የሁለተኛውና የአራተኛውን ኮር የያዘ ነበር፡፡ መሳሪያ አርባ በፍጥነት የሚተኩሱ መድፎች ከሀምሳ ሺ አርሳሶች ጋራ፣ ሀያ አምስት ሺ ጠመንጃና አውቶማቲክ መሳሪያዎች፣ ከአሥራ ሁለት ሚሊዮን ጥይቶች ጋራ፣ ሁለት መቶ ሺ የእጅ ቦምቦች፣ ሶስት መቶ ሰላሳ የጭነት መኪናዎችን ያካትት ነበር



የሠለጠኑ አስካሪስ ወታደሮች ከአካባቢው ተወላጆች የሚመለመሉ የኢታሊያ የቅኝ ግዛት የንጉሣዊ ጦር አባሎች ናቸው፡፡ በኤርትራ ብቻ ሳይሆን በሶማሊያም ተመሳሳይ የተወላጅ ወታደሮች ነበሩ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ሁለት መቶ ሺ የሚሆን የአሸዋ ከረጢት፤ ሶስት መቶ ሺ ኪሎ ጥምዝ ባለ ሾህ ሽቦ፤ ሀያ አምስት ሺ አካፋዎች፤ አሥራ አምስት ሺ መጥረቢያዎች፤ ስልሳ ሺ ኪሎ ዳይናሚት ከስማንያ ሬዲዮች ጋራ ነበራቸው፡፡

የደጃዝማች አያሌው መድፎች ስልሳ ጊዜ ከተኮሱ በኋላ አኩለ ቀን ላይ ድምፃቸው ጠፍቷል፡፡ የአየር ድብደባው የመድፎቹን ተሸካሚ ተሽከርካሪዎቻቸውን ሰብሮታል የአንደኛው አንዱን ሲሆን የሌላኛውን ሁለቱንም ነበር፡፡ መድፎቹ ማራኪዎቻቸውን ለአርባ አመት በታማኝነት ካገለገሉ በኋላ ጣልያኖቹ የመድፎቹን ከሃዲነት ያን ቀን በመበቀል ለእድሜ ልክ ፀጥ እንዲሉ አድርገዋቸዋል፡፡

የመድፎቹ ስባሪ ተይዞ ከኛ ጋራ እንዲጓዝ ተደርጓል፡፡ ምክንያቱ አልገባኝም፡፡

# ምዕራፍ አሥራ ስምንት

## ማፈግፈጉ ተጀመረ

የኛን ወደኋላ መመለስ ቆርጦ ለማስቀረት ከመረብ ተነስቶ ስለሚመጣው የጣልያን መካናይዝድ ክፍል ምንም አይነት መረጃ አልደረሰንም። (ከአራተኛው የጣልያን ኮር የተውጣጣ ነበር) መልከአ ምድሩ እንዳስቸገራቸው አላወቅንም። መንገድ ለመጥረግም አንድ ሺ ሁለት መቶ ነጭ መንገድ ሰሪዎች ይዘው ነበር። በመንገዱ ምክንያት አንድ ሙሉ ቀን ሳይንቀሳቀሱ ውለዋል። እኛም ያሉበት አካባቢ እንዳ ሰላሴ ሊሆን ስለሚችል ደህንነት ያለው መንገድ በደቡብ በአዲ ረሲ በኩል መሆን አለበት ብለን ወሰንን። መንገዱ ጠባብ ነበር። አስቸጋሪ ቁልቁለቶችም ነበሩት ቢሆንም ግን ጠላት እኛን ለመከተል አስቸጋሪ ይሆንበታል።

የጭነት ከብቶች እጥረት ጉዟችን አዘገየው። በመጨረሻዎቹ ሁለት ቀናት የአየር ቦምብ ድብደባ ከጠበቅነው በላይ ብዙ ሞቱብን። ህክምና ቡድኑ ከነበረው ዘጠኝ አህዮች አራት ብቻ ነበር የተረፉት።

በደጃዝማቹ ጥረት ችግሩ ወዲያውኑ በቀላሉ እንዲስተካከል ሆነ። ማንኛውም ትርፍ እቃ ወይም ንብረት እንዲቀር ተወሰነ። እኔ ራሴ ከነበረኝ ንብረት ከጦር ምርኮ በገንዘብ የገዛሁዋቸው ታይፕ መፃፊያና የሙዚቃ ማጫወቻ ፎኖግራፌን መተው ነበረብኝ። የቆዩ ሞዴል ጠመንጃዎች ጥይቶች በሙሉ በምስጢር መሬት ውስጥ እንዲደበቁ ተደረገ። የአካባቢው ገበሬዎች የተደበቀውን ንብረት ምናልባት አግኝተው ተከፋፍለውት ይሆናል ጣልያኖቹ ግን አላገኟቸውም።

በሶስት ሰአት ኮርቻችን ጫንን። አይን ማየት እስከሚችለው ድረስም ከፊትና ከኋላችን ሰዎችና ከብቶቻ በመስመር ይጓዙ ነበር። ብዙዎቹ ወታደሮች በውጊያው ያልተካፈሉ መሆናቸውን በቀላሉ ማየት እንችል ነበር። በደንብ ያረፉና ደህና ናቸው የተዝናኑ ይመስላሉ። ዝናራቸው ሙሉ ነው። ጠመንጃቸውም አዲስና እንደተወለወለ ነው። ጓደኞቻቸው ከጉልበተኛ ጠላት



ጋር ሀይለኛ ውጊያ ሲያደርጉ የት ነበሩ? ይህ በማያቋርጥ ሰልፍ የሚጓዘው ሰው በሙሉ ከሽንፈት የተረፈ ጦር ነው ብሎ ተመልካች ያስብ ይሆን?

አይደለም! በአስር ሺ የሚቆጠሩ አባት ሀገራቸው የጣለባቸውን እምነት የከዱ ወታደሮች ነበሩ። ጉልበታቸው ሳይደክም፤ የታጠቁትን ጥይት ሳይጠቀሙ ያሰቡ የነበረው እስከ አሁን ድረስ ካልተሸነፈ ጠላት ፊት ሸሽቶ መሄድ ብቻ ነበር። ማንም ያዘነ አይመስልም። ማንም ቢሆን ይህ ወደኋላ ማፈግፈግ ወይመ መሸሸት ለአቢሲኒያና ለህዝቦችዋ ምን ማለት እንደሆነ ያስተዋለ የለም። ይዘፍናሉ። ይቀላለዳሉ። ወሬ እያወሩ ሰላመለጡ ብቻ እርስ በርሳቸው እንኳን አወጣህ ይባባላሉ።

አልፎ አልፎ እነዚያ ውጊያው ላይ የነበሩ ሰዎች ሰላደረጉት ነገር ወይም ጓደኞቻቸው ሰላደረጉት ነገር ይፎከራሉ ጉራም ይነዛሉ። "ታውቃለህ ጣልያኖች ተጋድመው ከመሸጉበት ጉድጓድ ላይ ለማጥቃት ከመጀመሪያዎቹ አንዱ እንደሆንኩ"

"አንድ ሰላቶ የሙሶሎኒ በምብ ወረወረብኝ። ከዚያ ቀይ ኳሶች አንዱን፤ ሲወራ ሰምታችሁ ይሆናል፤ ጎንበስ ብዬ በላዩ አልፎ እንዲሄድ አደረግሁት፤ ዘልዬ የዚያን የተረገመ አንገት ቀላሁት! ደሙን ከጎራዴዬ መጥረጌ ነው እንጂ ታዩት ነበር። ካላመናችሁኝ ጓዴን በቀለን ጠይቁ። እሰቡት ብቻ የጣልያን አንገቱ ሲቆረጥ ሁል ጊዜ 'ማማ ሚያ' ብሎ ይጮሃል"

ሳቅና እንኳን ደስ ያለህ

ለመረዳት እንኳን የማያስቸግር የአእምሮ ለውጥ በነዚህ ሰዎች ላይ ሰፍኗል። ግዴታቸውን ባይፈፅሙ እንኳን እንዳው እጠገብ በሆኑም ይበቃ ነበር። አሁን ሁሉም ነገር አልቆለታል። የነበረባቸው ሸክም ተነስቷል እና ዕድለኞች ነን ብለውም ያስባሉ። እውነቱ ቢነገር እኛም ብንሆን በእንደዚህ አይነቱ አእምሮ አስተሳሰብ ተለከፈናል።

በአብዛኞች ሌሊቶቹ መድፎች ሲተኮስ የተተኮሰው እርሳስ ተራራው ላይ ሲያርፍ እንሰማለን። ብርሃን የሚያበሩ የምልክት ሮኬቶች በአድማሱ ላይ በተከታታይ ይበራሉ። የአፍ ጋጋ ማለፊያ በር አስከአሁን ክፍት ነው። ወታደሮች የቆሰሉትን ይዘው ይመጣሉ። ሌሎች ደግሞ በጨረቃ ብርሃን ተመልሰው የሞቱትን ይቀብራሉ።

ከአክሱም የሚመጣ መንገድ እኛ ካለንበት አንድ ማይል ርቀት ነው ያለው። ነገር ግን የኛን መመለስ ለመቁረጥ በተዘጋጁ የጣልያን ወታደሮች የተሞላ ነው። ወደ አንድ ሺ የሚሆኑ የኛ ወታደሮች ተሰብስበው ከሰላሳ

አውቶማቲክ መሳሪያ ጋራ ቀድመው ተላኩ:: አጋጣሚ ሆኖ ፍራቻችን ትክክል አልነበረም ሁሉም ነገር ፀጥ ያለ ነበር:: ያ ሁሉ ሰው እያለፈ እኛም ለብዙ ሰአታት ተኛን::

ፀሐይ ከመውጣቷ በፊት አንድ ቦታ ደረስን:: ደጃዝማች እዚህ ቦታ ዋሻ እንዳለ ያውቃሉ:: ስለዋሻው አንድ ገበሬ ሲጠየቅ ስለዚህ ነገር የማውቀው የለም ብሎ መለሰ ነገር ግን በአነጋገሩና ለኛ ጥሩ አመለካከት ሰላልነበረው ውነቱን እንዳልተናገረ ግልፅ ነበር:: በቀላሉ ምንም አይነት የሚጠቅም መረጃ መስጠት አልፈለገም:: ስለዚህ ለማናገር ክበድ ያለ ዘዴ መጠቀም ነበረብን::

ተያዘና በሽጉጥ አስፈራራነው፤ በአግሮቹ መሀል ሲተኮስበት የምር መሆኑ ገባው:: ከሁለት ደቂቃዎች በኋላም በሸለቆው ገደል በኩል ባለ ጠባብ መንገድ ተጉዘን ሰፊ የሆነ ሶስት መቶ ሰዎች መያዝ የሚችል ዋሻ ያለበት ቦታ ደረስን:: ከድንገተኛ ጥቃት ራሳችን ለመጠበቅ ወደ አንድ ሺ የሚሆኑ ወታደሮች ከዋሻው በላይ ባለ ቦታ ላይ እንዲጠብቁ ተደረገ:: ግን እራሳቸውን በድንጋዮች ጀርባና በቁጥቋጦች መሀከል መደበቅ ነበረባቸው::

ዋሻው ግን በአንድ በኩል ክፍት ስለነበር በችኮላ መጠለያ የሚሆን ግንብ ተሠራ:: የመጨረሻ ረድፍ ድንጋዮች እየደረደርን ነበር ልክ አውሮፕላኖቹ መተው የተለመደውን ሥራቸውን ሲጀምሩ:: በሺ ኪሎዎች የሚቆጠሩ የብረት ቁራጮችና ዳይናሚት ያለ ርህራሄ በመሰመር የሚጓዘው መንገደኛ ላይ ያወርዱ ነበር::

ሰዎች ከአውሮፕላኖቹ ጋራ ድብብቆሹ ሰልችቷቸዋል ደንዝዘዋልም:: ምንም የተለየ ነገር አላደረጉም:: ወደየቤታቸው መንገድ ስለጀመሩ እነዚህ የሰማይ ላይ አውሬዎች እንደፈለጉ ያድርጉ:: ያንድ ሰው ቀኑ ካልደረሰ አልደረሰም ማለት ነው:: ቀኑ ደርሶ ከሆነ ደግሞ መሮጥና መደበቁ ዋጋ የለውም:: አሁን ያለው አማራጭ በሚቻለው ፍጥነት ወደፊት ቀጥ ብሎ መጓዝ ብቻ ነው:: ወደፊት ወደ ሰላማዊ ጎጆ ቤት::

ጦርነቱ ካለፈ በኋላ  አንድ የኢጣልያ አየር ሀይል መኮንን ጋራ ተገናኝቼ ነበር:: መኮንኑ ያን ቀንና ተከዜን ስናቋርጥ በቦታው የነበረ ነው:: እንደሱ አባባል ምንም ሳያስቀሩ ሁሉንም እንዲደመስሱ ትዛዝ ተሰጥቷቸው ነበር:: ለነዚህ ያልሠለጠኑ ሰዎች ምንም አይነት ምህረት እንዳይደረግ:: ስለዚህ መኮንኖቹ ሀላፊነታቸውን ለመወጣት በሙሉ ስሜት ነበር የወጡት:: የሙሶሎኒን ሀይል ለመቃወም የደፈሩ ሰዎች የሙሶሎኒን ክባድ እጅ መቅመስ ነበረባቸው::



ነገር ግን በነዚህ ሀይለኛ ቦምቦች ምክንያት የሚደርሰውን ጥፋት በተለይ ምንም መከላከያ በሌላቸው ሰዎች ላይ የደረሰውን የብዙሃን ሕይወት መጥፋት ሲመለከቱ በሚቀፍ ስሜት ከመጀመሪያው ተውጠው ነበር:: መኮንኑም እኔም በራሴ

"እቁም! አሁንስ ይበቃል ብዬ" ጮኬ ነበር::

ነገር ግን ትዛዝ ትዛዝ ነው መፈፀም ነበረበት:: እነዚህ ምስኪን ሰዎች እንዳው ለመሮጥ ወይም ለመደበቅ ቢሞክሩ ምን ነበረበት:: ነገር ግን ዝም ብለው መንገዳቸውን ቀጠሉ እንደ ታዛዥ ልጅም ራሳቸውን ለመጣባቸው ነገር ሁሉ ሰጡ::

ብዙ ቦምቦች ከመንገዱ ዳር ራቅ ብለው መውደቃቸው በአብራሪዎቹ የሰብአዊነት ስሜት ምክንያት ይሆን? አቢሲኒያውኖቹ ቦምቦቹን አርቆ ስላስጣለላቸው ቅዱስ ጊዮርጊስን አመሰገኑ እኔ ግን ያመንኩት የምህረት አምላክ ምህረት የሚያሳዩትን ይከሳል ብዬ ነው::

ያን ቀን ዘግየት ብሎ አብራሪዎቹ የእሳት ቦምቦች በመጣል ራሳቸውን ሰላረኩ በመንገዱ ዙርያ የነበረው ሳር ለብዙ ኪሎሜትሮች ርቀት በእሳት ይነድ ነበር:: ለክብቶቹ የሚሆን ግጦሽ ሰሰሌለ ወታደሮቹ መንገዳቸውን ያለማቋረጥ ዝም ብለው ለመቀጠል ተገደዋል:: በተጨማሪም ለመከላከል የነበረውን ስሜትና ችሎታንም ቀንሶታል::

ከጠዋቱ አራት ሰአት ሲሆን ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለ አንድ ወታደር ሲሮጥ መጣና ጣልያኖቹ ለማጥቃት መንገድ ላይ መሆናቸውን ተናገረ:: ጣልያኖቹ በመኪናዎች ላይ ነው የነበሩት ምክንያቱም ስፋት ያለው የአቧራ ጉም በፍጥነት ሲጓዝ ታይቶአል:: ጭንቀት ተፈጠረ:: ሁሉም ወደ ውጭ ይሮጥ ጀመር:: ማንም ሰው ዋሻው ውስጥ እንደሆነ መያዝ አልፈለገም ነገር ግን ወደ የት ወይም በየት አቅጣጫ ነው የሚኬደው?

በጠባቡ መንገድ በአንድ ጎኑ መቶ ሜትር ከፍታ ያለው ገደል በሌላ ጎኑ ደግሞ ተመሳሳይ ቀጥ ያለ ገደል ባለበት መቶ የሚሆኑ የተደናገጡ እርስ በራሳቸው የሚጮሁ ሰዎች ቆመዋል:: እጃቸውን ያወዛውዛሉ እይተገፋፉ ይጨናነቁ ነበር:: ሁሉም ሀሳብና ምክር ሰጪ ነበር:: ግን የሚረባ አልነበረም:: እንግዲህ አውሮፕላኖቹ ቢኖሩም እራሳችን ወደ ሜዳው ወጥተን ጠላትን በመቋቋም የቀረውን ጦር ማዳን እንችል ይሆን? ወይስ በነበልባሉና

በሚነደው እሳት መሀከል  እየተሳብን ቁልቁል ሄደን ከሸለቆው ስር ደርሰን ተከዜን እንሻገር ወይ? ሌላ አማራጭ በፍፁም አልነበረም፡፡

የሰማንያ አመት ሽማግሌ የሆኑት ፊታውራሪ እሉላ ጎራዴያቸውን መዘው "ዘራፍ አድዋ ! ትዝ ይበልህ አድዋ" እያሉ ጮሁ፡፡ ትውልድ ቦታቸውን ትተው የመጡት በዚህ በተቀደሰ ጦርነት ተካፍለው በመሞት ገነት ለመግባት ነው፡፡ ትናንትናም ቢሆን እፍ ጋጋ ላይ ፊት መሰመር ሆነው ተዋግተው ነበር፡፡ ነገር ግን ሞት ሊወስዳቸው የተፀየፈ ይመስላል፡፡ ዛሬ ቀናቸው ደርሷል፡፡ አብረዋቸው የሚዋጉ አንድ መቶ ሰዎች ቢያገኙ ደጃዝማችና ራስ አምሩ በደህና እስከሚያመልጡ ጠላትን ወጥረው መያዝ ይችላሉ፡፡

ሽማግሌው ኮሰተር ያለ ቁም ነገር ነው የሚናገሩት በሰሜት ሰውነታቸው ሲንቀጠቀጥ ምራቃቸውም በፂማቸው ላይ ይፈናጠር ነበር፡፡  ነገር ግን በጣም እየከፋቸውና እያዘኑ በጩኸት እንዲቀመጡ ሆነ፡፡ ሀሳባቸው ተቀባይ አላገኘም፡፡ በመጨረሻም ጠባቂ ዘቦች ጣልያኖችን ለመከላከል ሲሞከሩ የጦር አዛዦችና እኛ ከሥራችን ባለው ሸለቆ አድርግን ወደ ተከዜ ለመሸሽ አንድንሞክር ተወሰነ፡፡

ሰለዚህ ምክር ዶክተሩ ምንድነው ያሰበው?

"እዎ በርግጥ፡፡ ነገር ግን መጀመሪያ ጣልያኖቹ እኛን ሲያጠቁ እንደመጡ ማረጋገጥ የለብንም ወይ? እንደዛም ሆኖ ሾልኮ ለመሄድ በቂ ጊዜ አለን"

ገና ተናግሬ ሳልጨርስ አሳሽ ወይም ቃኝ እውሮፕላን ቀጥታ በሸለቆው በላይ መጣ፡፡ በዚህ ግርግር መሀል ሰዎች ወደ ዋሻው መግባትና መውጣት ሲጀምሩ ታየንና የአነጣጥሮ ተኩዋሽ ኢላማ ሆን፡፡ ጥይቶቹ አለቶች ላይ በሚያለቅቅ ድምፅ ይነጥራሉ፡፡ ሁላችንም አንዱ ባንዱ ላይ እየተደራረብን መሬቱ ላይ ተነጠፍን፡፡ ተነሰተንም ሮጥን ወደ ዋሻው ለመግባት ከፊት ለፊታችን የዋሻ መግቢያ መንገዱን የዘጉ ሰዎች እስኪለቁ ድረስ በዛው ሁኔታ መቆየት ነበረብን፡፡ የሚገርም ሁኔታ ነበር፡፡

እንደእድል ሆኖ የገደሉ ግድግዳ ሰለሚሸፍነን አውሮፕላኑ በተመላለሰ ቁጥር እንታይም ነበር፡፡ ሰለዚህ ጉዳዩ ወደ ዋሻው መግባት መቻል ነው፡፡ ሁሉም ገብቶ ሲያበቃ ሁለት ሰዎች ብቻ ቆሰለው ተገኙ፡፡

አውሮፕላኑም ያየውን ሪፖረት ለማድረግ ተመልሶ ጠፋ

የኔ ሃሳብ ተሰሚነት እገኘና አንድ መኮንን ተላከና ከአንድ ሰአት በኋላ ተመልሶ መጣ፡፡ ምንም አይነት የጠላት ጦር አላየም፡፡ በግርግሩ ንብረታችን ለመዝረፍ አሰበው ይሀን ውሸት ወሬ ያሰወሩት ለካስ ገበሬዎች ናቸው፡፡



አውሮፕላኖቹም መጡ ነገር ግን የሚጥሉት ቦምብ ኢላማውን እላገኘም፡፡ ቦምቦቹ ወይ ሸለቆው ወሰጥ አለዚያም ከገደሉ አናት ላይ ነበር የሚወድቁት፤ ከገደሉ አናት ላይ ሲወድቁ ግን የአለት ሰባሪ ድንጋዮች ቁልቁል ይወርዱ ነበር፡፡

ተዋጊ አውሮፕላኖቹ ደግሞ የባሱ ነበሩ፡፡ እንዳበደ ሰው አውቶማቲክ መሳሪያቸውን እየተኮሱ ወደኛ አቅጣጫ ልክ ወደ ዋሻ ውሰጥ እንደሚገቡ ሆነው ይበራሉ፡፡ ከዛ በመጨረሻው ሰከንድ ወደ ላይ ቀጥ ብለው ይበሩና ተገልበጠው በጀርባቸው ለብዙ ሜትሮች ከሄዱ በኋላ  እንደገና ተገልብጠው ተመልሰው ይመጣሉ፡፡

እንዳንድ ጊዜ በጎናቸው እንደሆኑ ይመጣሉ፡፡ የተለመደ የአክሮባት ትርኢት ነበር፡፡ በሰላም ጊዜ ቢሆን እንደዚህ አይነቱን በረራ ለማየት በከፈልኩ ነበር፡፡

ይህ ሁሉ አንድ ሰአት የፈጀ ትዕይንት ሲካሄድ እኛ ወይም እንቀመጣለን ወይም ከግድግዳው ጀርባ ተጠቅልለን እንጋደማለን፡፡ የሚተኮሱት ጥይቶች አለቱን ወይም ግንቡን እየመቱ ይፈናጠራሉ፡፡ ትልቁ አደጋ ደግሞ እንደዚሁ ከሚነጥሩት ጥይቶች ነበር ከውጭ በኩል እልፎ አልፎ ወደ ውሰጥ ይገቡ ነበር፡፡

ከአሰቃቂው የቦምብ ድብደባ ጋራ ሲወዳደር ይኸኛው ጨዋታ ነበር፡፡ እየቀለድንም ነበር፡፡ ጓደኞቻችን አጠገባቸው ጥይት የዋሻውን ግድግዳ ወይም ጣራ ሲመታ እንዴት እንደሚሆኑ እያነሳን እንሰቅና እንቀልድም ነበር፡፡ አራት ሰዎች ብቻ ቀላል ቁሰል መቁሰላቸው ራሱ የሚገርም ሁኔታ ነበር፡፡

ከቀኑ አሥራ አንድ ለአት ሲሆን ጣልያኖቹ እየመጡ እንደሆነ የሚገልፅ አዲስ ዜና መጣ፡፡ ተኩሰ ድምፅ ይሰማ ጀመር፡፡ ወዲያውኑ ከላይ ከሜዳው ላይ ያሉ የኛ አውቶማቲክ መሳሪያዎች መንፈቅፈቅ ጀመሩ፡፡ ያለምንም ጥርጥር አንድ ነገር ሊሆን ነው፡፡

አሁን ግን ምንም ግራ የሚጋባ ነገር የለብንም፡፡ ቀኑን መንገድ ሰንፈልግ በሜዳው በኩል አደርጎ በዋሻው ደቡብ አቅጣጫ የሚወሰድ ሌላ መንገድ አግኝተናል፡፡ እንዴት ያለ መንገድ! ቀጥ ባለው ገደል በድንጋዮች ላይና በከፍተቶች በኩል ወደ ላይ መቶ ሜትር የሚሆን ከፍታ ወደ ሰማይ ይወጣል፡፡ በጣም መጠጋጋታችን የሚረዳ ነገር ሆነ፡፡ እኔ ራሴ እንኳን ጉልበታቸው በጠነከረ ሰዎች ትከሻ እየተረማመድኩ ነው ወደ ላይ ያወጡኝ፡፡ ከታች ከሰር ያሉት እንዴት አድርገው የሰዉን ሁሉ ከብደትና ጭነት ችለው

ከዚያም በመጨረሻ እራሳቸው ተከትለውን እንደወጡ ለመረዳት አስቸጋሪ ነው፡፡

ወደ ላይ በምንወጣበት ጊዜም የተኩስ መጠን ጨመረ፤ ጥይቶች እያፏጩ በአናታችን ላይ ያልፉ ነበር፡፡ ከላይ ከሜዳው ለመጀመሪያ ጊዜ ላይፈሩ ወደፊት የሚገፉ በርከት ያሉ ሰዎች አየን፡፡ አሁንም አሁንም በጥይት ሲመታ ወዲያው የሚቀመጥ ወይም ደግሞ የሚወድቅ ሰው አያለሁ፡፡ እንደዛም ሆኖ ሰዎቹ ሳያቆሙ የቆሰሉትን ያነሱና በበቅሎ ይጭኑ ነበር፡፡

በሰሜን አቅጣጫ የኛ ወታደሮች ተጋድመው ጠላት ላይ ይተኩሳሉ፡፡ ጠላት እኛ ቆመን ከነበርንበት ቦታ አንድ ኪሎሜትር ርቀት ላይ ጠምዶ ተቀምጧል፡፡ አውቶማቲክ መሳሪያ ቢኖረውም በብዙ ምክንያቶች ይህ ጠላት በርግጥ የጣልያኖች ጦር ነው ብዬ አላመንኩም፡፡ ገበሬዎቹ ነበሩ፡፡

በምሥራቅ በኩል መልሰን በማጥቃት ከግማሽ ሰአት በኋላ ወደ አምስት መቶ የሚሆኑ ገበሬዎችን ማባረር ቻልን፡፡ የሞቱባቸውን ሰላሳ ሰዎች ጥለው ሄዱ፡፡ ከእንደዚህ አይነቱ አዲስ ድንገተኛ ጥቃት ለመከላከል የደጀን ወይም የኋላ ጦር ለማዘጋጀት መቆም ነበረብን፡፡ ከምሽቱ ሶስት ሰአት ሳይደርስ የሰላሳ ኪሎሜትር ርዝመት ያለው የተጓዥ ሰዎች መሰመር አልፎ ከሄደ በኋላ ጉዟችን ጀመርን፡፡

ያን ሌሊት በሸሬና በዛና መሀከል ባለው ቀጥ ባለው የገደል ቁልቁለት ብዙ ሰዎችና ከብቶች እየወደቁ አለዚያም እየተረገጡ ሞቱ፡፡ አሁንም አሁንም በአለቶቹ መሀል በደንብ የተደበቁ ገበሬዎች ይተኩሱብን ነበር፡፡ ነገር ግን እንደሚወራባቸው ፈሪነታቸው ምስክርነት ደግሞ አውቶማቲክ መሳሪያ ስናረበርብባቸው ወዲያው ጥለው ይጠፉሉ፡፡

እኩለ ሌሊት ሲሆን በመሀል ዛና የሚገኙ ሁለት ትልልቅ ዋሻዎች ያሉበት ቦታ ደረስን፡፡ እዚህ ቦታ ላይ ለአንድ ቀን ቢሆን አቁመን ጠላትን ለመከላከል እንድንሞከር ተወሰነ ነገር ግን ወታደሮቹን እንዲቆሙ ማሳመን ብንችል ነበር፡፡

ማረፍ መቻል እንዴት ጥሩ ነገር ነበር፡፡ በሶስት ቀናት ውስጥ ተደምሮ ሰድስት ሰአት የሚሆን እንቅልፍ እንኳን አልተኛንም ስለዚህ ድካም አያሸነፈንም ነበር፡፡ ምግብም ቢሆን ለሃምሳ ሰድስት ሰአታት በሚሆን ጊዜ ውስጥ የቀመሰነው ነገር አልነበረም ወደፊትም ቢሆን የሚበላ ነገር መኖሩ አይታወቅም፡፡ በመንገዱ አቅራቢያ የነበሩ ጥቂት ገበሬዎችም ቢሆኑ የነበራቸውን ምግብ አሸሽተው ጥለው ሄደዋል፡፡ የራሳችን የጭነት ከብቶችም የት እንዳሉ ማወቅም አይቻልም ነበር፡፡ ለኔ ከፉው ነገር ግን ትምባሆዬ ማለቁ ነበር፡፡



# ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ

## በሞት ወጥመድ መሀከል

ከተጠለልንባቸው ከሁሉም ዋሻዎች ሁሉ ሁለቱ የዛና ዋሻዎች በማንኛውም ረገድ የበለጡ ነበር፡፡ ጠባብ የሆነ የሀምሳ ሜትር ማለፊያ ሁለቱንም ያገናኛል፡፡ ውጭ ካለው የአመድ ከምርና ውስጥ ደግሞ የሚታዩትን ቁፋሮዎች ሳይ ዋሻዎቹ ከጥንት ጀምሮ ሰዎች ይኖሩባቸው እንደነበር ማስተዋል ይቻላል፡፡ የመቆፈሪያና የመሮ ቅርፆች በተጠረቡት ድንጋዮች ላይ ማየትም ይቻላል፡፡

የትልቁ ዋሻ መግቢያ ከፍ ያለ ጣራ ወዳለው ሰፊ አዳራሽ ክፍል ያመራል፡፡ ውስጥ ሆኜ ስናገር የሚነጥረው ድምፅ ትልቅ የድሮ ቤተክርስቲያን አዳራሽ ያለሁ ነው የሚመስል፡፡ በሶስት በኩል ወደ ውጭ የሚወስዱ ማለፊያዎች አሉ ርዝመታቸው ተደምሮ አንድ ኪሎ ሜትር ይሞላል፡፡ የተቆፈሩ ክፍሎች፤ ኪስ ቢጤ ቦታዎች እና ጥርቦች ይታያሉ፡፡ ከነዚህም በተጨማሪ ወለሉ ላይ የተቆፈሩ ጉድጓዶችም ነበሩ፡፡ በኋላ በጉድጓዶች ውስጥ ብዛት ያለው የገብስና የአተር ክምር አገኝተን ወዲያው አውጥተን ቀቅለን በላን፡፡ ዋሻው ውስጥም የምንጭ ውሃ ነበር፡፡ በጥንቃቄ ለተጠቀመበት ለአንድ ሺ የሚሆን ሰው ይበቃ ነበር፡፡ የከብት ማደሪያው እራሱ አስር ከብቶች ማላደር ይችላል ከድንጋይ የተጠረበ የከብት ማብያም ነበረው፡፡

የተናፈቀው እንቅልፍ ረዥም ጊዜ አልቆየም፡፡ በሺዎች የሚቆጠሩ ቁንጮችና ትኋኖች በቁማችን ነው የበሉን፡፡ ውጭ መተኛት ደግሞ አልቻልንም ብርዱም ሀይለኛ ነበር ብርድ ልብሰም አልያዝንም፡፡

ፀሀይ እንደወጣች አውሮፕላኖቹ ለተለመደው ሥራቸው መምጣታቸውን አሰታወቁ፡፡ ጥቂት ከጣሉዋቸው የፈንጂ ቦምቦች ውጭ የአላት ቦምቦችን በመጣል ነው ያተኮሩት፡፡ አካባቢው በሙሉ በአላት ይንቦገቦግ ጀመር፡፡ ይህ ዘዴያቸው የሚሠራ ሆኖ ተገኘ፡፡ ማንም ሰው በመቆየት ከብቱ በረሃብ ሲሞት ማየት አልፈለገም ሰለዚህ በዚህ ሁኔታ ብቻ

ጠላትን ለመቋቋም ያሰብነው ዕቅድ በሙሉ ተበላሸ፡፡ ያለን አማራጭ መቀጠል ብቻ ነበር፡፡ ከተቻለ በተከዜ ሸለቆ ማዶ ሆነን ራሳችን መከላከል ነው፡፡ እንግዲህ የትግራይ ክልልን እንዳጣነው አድርገን መቀበል ነበረብን፡፡

ሁኔታዎች እዚህ ደረጃ ሲደርሱ ጣልያኖቹ የትግራይን መሬት በመውሰዳቸው የሰላም ካሳ ነው ብሰው ቢረኩና ቢበቃቸው አንድ ነገር ነበር፡፡

ፀሀይ እንደጠለቀች ማምሻውኑ ባለ ብዙ ሞተር ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች ከደቡብ ተነስተው እኛን አልፈው ሲበሩ አየን፡፡ ወዲያውኑ ሁለት ተዋጊ አውሮፕላኖች ጎን ለጎን በሰአት አራት መቶ ኪሎ ሜትር በሚሆን ፍጥነት እየተጣደፉ ከነፉ፡፡ ለምን?

ቆየት ብሎ አመሻሽ ላይ ያን ቀን በእኩለ ቀን ጣልያኖቹ ፊት ፊት በመስመር የሚጓዘውን መንገደኛ የተከዜ መሻገሪያ ላይ እንደበደቡት ሰማን፡፡ ውጤቱም እንደተባለው ከሆነ በጣም አሰቃቂ ነበር፡፡

ለነገ ለብዙሃን ጭፍጨፋና እልቂት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑ ግልፅ ሆነ፡፡ እነዛ ተዋጊ አውሮፕላኖች እየተጣደፉ የሄዱበት ምክንያትም ግልፅ ሆነልን፡፡ በጊዜ ሪፖርት አቅርበው ወድያውኑ ትዛዝ እንዲሰጥና አውሮፕላኖቹ በነጋታው በምብ እንዲጫኑ ነበር፡፡ በነሱ ቤት እነዚህ የጫካ ሰዎች እንደ አይጥ በየቦታው ተደበቀው ስለነበር ያ የተጣሰው ሁሉ በምብና የጠፋው ነዳጅ እስካሁን ድረስ በከንቱ ነበር፡፡ አሁን ግን ያለምንም መከላከያ ወጥመድ ውስጥ ገብተዋል፡፡ ከዚህ የበለጠ ጥሩ አጋጣሚስ ይኖራል ብሎ የሚመኝ አለ? በሚቀጥለው ቀን ቦምቦች በከንቱ አይወድቁም ምክንያቱም መረጃ አቀባዮቻችን እንደነገሩን ከሆነ ከዛና ጀምሮ ተከዜ ሸለቆ ማዶ ድርስ ያለው መንገድ መላወሻ በሌለው የሰዎችና የእንስሳት መንገደኞች ተጨናንቋል፡፡

በሌሊት እያንዳንዱ ሰው በሚቻል ፍጥነት ወንዙን መሻገር ይፈልጋል፡፡ እኛም ብንሆን ተመሳሳይ ፍላጎት ስለነበረን ማለፍ የማይቻለውን ዋና ቀጥተኛ መንገድ ትተን ወደ ተከዜ የሚወስድ ዙሪያ ጥምዝ መንገድ እንድንወስደ ሆነ፡፡ በፈጣን እርምጃ ከተጓዝን ቦታው ላይ ልክ እኩለ ሌሊት እንዳለፈ እንደምንደርስ ገምተናል፡፡

የሚያታልል ተስፋ

አስቤው ከማውቀው በላይ በጣም አስቸጋሪ መንገድ መሆኑን መግለፅ ብቻ አይበቃም፡፡ መንገዱ ከአንድ ከደረቀ ወንዝ ዳርቻ አሸዋማ ቦታ ሲደርስ አለቀ ተሰወረ፡፡ ያገኘነው ገበሬ መንገድ አመላከተን ግን ወዲያው ሲሰውር



አሳስቶ ወዳልሆነ ቦታ እንደመራን ገባን፡፡ ወደኋላ ተመልሰን ትክክለኛውን መንገድ ማግኘት አማራጭ የሌለው ነገር ነበር፡፡ ያን ቀን ማታ የዚያ መንገድ የጠቆመን ገበሬ ቤት በእሳት ሲጋይ ቂም በቀላቸውን በመወጣታቸው ደስ ያላቸው ሰዎች ነበሩ፡፡

ቁሸሸ ብለን በላብና ከዛፎችና ከቁጥቋጦች ጋራ እየተጋፋን ስንመጣ ከለበስነውን ጥላሸት ጋራ ከጥዋቱ አሥራ አንድ ሰአት ሲሆን ተከዜ ሸለቆ ደረስን፡፡ ሸለቆው የ ላቲን ፊደል ቪ "V" ቅርፅ ያለው ሆኖ ወደ ታች አንድ ሺ ሜትር ጥልቀት አለው ከታች ደግሞ የወለሉ የጎን ስፋት ከአስር ሜትር አይበልጥም ነበር፡፡ መንገዱ ቁልቁለታማ በሆነ የተሸረሸረ አለት ላይ በጎንና በጎን ቀጥ ባለ ገደል ግድግዳ ታጅቦ ወዲያው ይታጠፍና ሰላሳ ሜትር ስፋት ወዳለውና አንድ ሜትር ጥልቀት ወዳለው ወንዝ ውሀ ይወርዳል፡፡ በዚህ ቦታ ላይ የደከማቸው ሰዎችና እንስሳት ተጨናንቀው በፍጥነት ይጓዛሉ፡፡ መንገዱም ቁልቁል ነው፡፡ ከወንዙ ማዶ ደግሞ ቀጠን ባለ መስመር እነስ ያለ የሰው ቁጥር እየተንፏቀቀ በገደሉና በጠባብና በተጠማዘዘው መንገድ ወደ ላይ ሲወጣ ይታያል፡፡

ከታች ከወንዙ ዳርቻ ከጩኸት ጋራ የተኩስ ድምፅ ይሰማል፡፡ ከመሻገሪያው ቦታ አካባቢ ያሉ አዞዎችን ለማስፈራራትና ለማሸሽ ነበር፡፡ ፈዘዝ ባለው በጥዋት ብርሃን የሚታየው አስፈሪና አሰቃቂ ትዕይንት ከዳንቴ ዲቫይን ኮሜዲ (Dante's Divine Comedy) መፅሀፍ ውስጥ ከተፃፈው የገሃነም ትዕይንት ጋራ ይመሳሰላል፡፡

ለጥቂት ጊዜም የስንፍናና የመሸነፍ ስሜት ተሰማኝ፡፡ ያሰኝ ጉልበት በወንዙ ማዶ ያለውን ገደል ለመውጣት ያስችለኝ ይሆን? እንደያው ትንሽ አረፍ ማለት ብችል

"ሀኪም! እዛው አትቁም ና አብረህ ሂድ! የምናባክነው ጊዜ የለንም! " ጥሪው ከደጃዝማች ስለነበር ወዲያውኑ አነቃቃኝ፡፡ ደጃዝማች ከአንድ የጭነት ከብት ኮርቻ በጎራዲያቸው ማንገቻ የሚሆን ቀበቶ በጥንቃቄ ከቆረጡ በኋላ ቅርጫቶችን አነሱና ለወታደሮች እንዲሸከሙ ሠጡ፡፡ ወደ ኔ ዞር ብለውም "ቢያንስ ቢያንስ ለዛሬ የምንበላው ምግብ አለን፡፡ ና! " አሉ፡፡

ከጭነት በቅሎአችን አንዱ ተገኘ፡፡ ረሃባችን ለማስታገስ እድል መገኘቱ ሁሉንም ነገር ብሩህ ተስፋ ሰጠው፡፡ ነገር ግን የደጃዝማችን ትዛዝ መከተል ማለት ደግሞ ሌላ ጣጣ ነበር፡፡ የኔ የግል ሠራተኛ ስለጠፉብኝ የራሴን በቅሎ እራሴ መምራት ነበረብኝ፡፡ ቀጥ ባለው የቁልቁለት መንገድ መጋለብ አይቻልም

ነበር፡፡ በቅሎዋን በልጓሙ እየጎተትኩ ስሄድ በቀጠነው ሰውነትዋ እንኳን ሰትስበኝ የምንትትበት ከንዴ ከመታጠፊያው ወልቆ የወጣ ነበር የመሰለኝ፡፡ በቅሎዋን እየጎተትኩ ደግሞ ባለኝ ሀይል በሙሉ ፊት ለፊቴ ያሉ ሰዎችንና አመፀኛ እንስሳቶችን እየተጋፋሁ ማለፍ ነበረብኝ፡፡

ሳስተውል ከጓደኞቼ ተነጥዬ ብቻየን ቀርቻለሁ፡፡ ቀስ ብዬ እየተሳብኩ ከወንዙ ለመድረስ አጋማሽ መንገድ ላይ ደረስኩኝ፡፡ እዛ ስደርስ ደግሞ መንገዱ ሙሉ በሙሉ በራስ አምሩ ሰዎች ተዘግቷል፡፡ ሰዎቹም ሊያሳልፉኝ አልፈቀዱም፡፡ የኛ ሰዎች ቢሆኑ ኖሮ ያሳልፉኝ ነበር፡፡ አመፀኛዋ በቅሎ ወደኋላ እየሳበችኝ ደጃች አያሌውንና እሽከሮቻቸውን ልደርስባቸው እንደማልችል ግልፅ ሆነለኝ፡፡ ፀሀይ መውጫም እየተቃረበ ነበር፡፡ በዛ ሰአት ውስጥ ከጓደኞቼ ጋራ ካልተደባለቅሁ በአደጋ ጊዜ የሚደርስልኝ ሰው የለም፡፡ ስለዚህ በቅሎዋን እንደ ዕድሏ ትሁን ብዬ ለቀቅኳት፡፡

በጠመዝማዛው መንገድ ከአንዱ መታጠፊያ ወደ ሌላው መታጠፊያ እየዘለልኩ ቁልቁል ወረድኩ፡፡ ቀስ እያልኩም ብዙ መንገድ ሸፈንኩ፡፡ በላብና በአቧራ ተሸፍኜ የሚያስቅ ፊት ሳላሳይ አልቀረሁም ምክንያቱም ባለፍኩ ቁጥር ሰዎች እየሳቁ "ተመልከቱት" ይሉ ነበር፡፡ አንድ ቦታ ላይ ስደርስ ዘጠኝ ሜትር ከፍታ ያለው ጉብታ ላይ ስዘል ድንገት ጠመንጃውን እያቀባበለ የሚጮህ ሰው ድምፅ ሰማሁ

"ያውና! ነጭ ሰው እየዘለለ ነው! እንዳያመልጥህ!"

ገና ሽጉጤን መዝዤ ዞር ከማለቴ በፊት ወዳጄ እቶ ማሞ ሊረዳኝ ሲጣደፍ መጣ፡፡ መጀመሪያ ሰውየው ላይ ድንጋይ ወረወረበት፡፡ ከዛም ነጎድጓድ በመሰለ ድምፅ "ትነካውና መሞቻህ ነው!"

ሕይወቴን አተረፈልኝ አለበለዚያ በምንም መንገድ ራሴን መከላከል አልችልም ነበር

ራሰና ደጃዝማች በየበቅሏቸው ልክ ውሀውን ሊያቋርጡ ሲሉ ደረስኩባቸውና ለደጃች አያሌው የምጋልበው ከብት እንደሌለኝ ተናገርኩ፡፡ በምልከት ከወጣቱ የወንድማቸው ልጅ ኋላ እንድፈናጠጥ አሳዩኝ፡፡

የነበረኝ ጉልበት በሙሉ ተሟጦ ነበር፡፡ ትንፋሽም እያጠረኝ ልቤ በፍጥነት እየመታ የሚንቀጠቀጡ ጉልበቶቼ ሰውነቴን መሸከም እቅቷቸው ነበር፡፡ ጆሮዎቼ ደንቁረዋል አፌና ጉሮሮዬ በአቧራ ተሞልቶአል ከዚህ የባሰ ደግሞ የውሃ ጥሙ ያቃጥለኝ ነበር፡፡ እንደምንም ታግዬ በቅሎዋ ላይ ወጣሁ፡፡



በወንዙ ውሀ መሀል ስንጓዝ ቀዝቃዛውን የወንዙን ውሀ መጠጣት የምችል መሰለኝ፡፡ ደጋግሜ አጎንብሼ በአጄ ውሀውን ለማፈስ ያደረግሁት ሙከራ እልተሳካም፡፡ በፍጥነት የሚወርደው ውሀ ደግሞ ያዞረኝ ጀመር፡፡ ይህንን የተመለከተና ችግሬን ያየ ወታደር የምጠጣው ውሀ በቅል ሰጠኝ፡፡ ሁለት ሆዳቸው የተቀደደ የሞቱ በቅሎዎች ወንዙ ወስጥ ነበሩ ነገር ግን የጠጣሁት ውሀ ጉሮሮዬን ሳላረጠበልኝ ከመጀመሪያው አሰቃቂ ነገር በማየቴ ሰውነቴን ሊያንቀጠቅጠው የነበረውን ሁኔታ አስረሳኝ፡፡

የሞተር ድምፅ መስማት ስንጀምር ገና የወንዙ ማዶ አንኳን አልደረሰንም፡፡ ደጃዝማች ለጥቂት ሰከንዶች ቆም እሉ ዙሪያውን ካዩ በኋላ ተከተሉኝ በሚል ድምፅ ተመለሱ፡፡ ተመልሰው ወደ መጣንበት ሄዱና መቶ ሜትሮች የሚሆን መንገድ ቁልቁል በወንዙ ከሄድን በኋላ  ከበቅሎዎቹ እንድንወርድ ትዛዝ ተሰጠ፡፡

በፍጥነት ሁኔታዎችን በማስተዋል ችሎታቸው ከገደሉ ግድግዳ ወደ ፊት ወጣ ያለ መቶ ሜትሮች ርዝመት ያለው አለት አይተው ነበር፡፡ እኛም በዚህ ወጣ ባለው አለት ስር ተጠለልን፡፡ በፍጥነትም ድንጋዮች ሰበሰብንና ግማሽ ሜትር ከፍታ ያለው መከለያ ሰራን፡፡ መጠለያው ሰፊ አልነበረም ተጨናንቀን ስምንት ሰዎች ብቻ ነው መያዝ የሚችለው፡፡ ሌሎቹ ተበትነው ለየራሳቸው መጠለያ ወይም መደበቂያ መፈለግ ነበረባቸው፡፡ ከፊት ለፊታችንና ከጎን የሰራነው የድንጋይ ካብ መከለያ ስለሆነ ተረጋግተናል፡፡ ዋናው መጠለያ ግን በአናታችን ላይ ወጣ ብሎ እንደ ጣራ የሚሸፍነን አለት ነው፡፡

ወደ የመደበቂያችን ቦታ ለመግባት እንኳን በቂ ጊዜ ሳናገኝ አሥራ አራት ባለ ሶስት ሞተር አውሮፕላኖች ተቃረቡ፡፡ ቀስ እያሉ በሸለቆው ላይ ይበሩ ጀመር፡፡

ጭልፊቶች፡፡ ለመሰየም አንኳን ጆፌ እሞራ ሳይሻል አይቀርም የሚያድኑትን በደንብ ያውቃሉ

ምንም ማምለጫ አልነበረም

ለምንስ ግዳዮቻችው ገና በሞት ፍርሀት ሊጠማዘዙ ማየቱን እንኳን ኢያስደስታቸውም?

በመጨረሻም ከደቡብ በኩል በመሀከላቸው የሚበቃ ከፍተት ፈጥረው በመስመር መጡ፡፡ መሪያቸው አንድ ቦምብ በደቡብ ከፍታ ላይ ሌላ ደግሞ መሀከል ላይ እንደገናም ሶስተኛ በሰሜን አቅጣጫ ከፍታ ላይ ጣለ፡፡ ሁሉም መንገዱ ላይ ወደቁ አላማውም እሱ ነበር፡፡ መንገዱ ለመተላለፊያ እንደማይሆን ማድረግ፡፡

ያ መግቢያ ወይም መተዋወቂያ ነበር

ከዚያ በኋላ ሁሉም በየተራ ይመጡ ጀመር፡፡ በምብ በቦምብ እየተከተታለ ከአሥራ እራቱ እውፕላኖች ይወርድ ጀመር፡፡ ሁለት ኪሎሜትር ርዝመት በማይሞላ ቦታና በሰዎችና በእንስሳት በተጨናነቀ መንገድ ላይ በሚያሰፈራ ሁኔታ ኢላማው ትክከል ነበር የሚያርፈው፡፡

በሽሰቆው ከሚነጥረው የገያል ማሚቶ ጋራ ጆሮ የሚያደነቁር ድምፅ ነበር

ልብ የሚያሰጨንቅ የህፃናትና የሴቶች ጩኸት ከዚያም በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ድምፅ ወደ ላይ ወደ መንግስተ ሰማይ ሲማፀኑ ይሰማል "በከርሰቶሰ ፈጣሪ እባከህ ምህረቱን አውርድልን!"

እሰቃቂ ኢሰብእዊ "ሥልጣኔ"

እኛም በሠራነው ግንብ ጀርባ ስር ተንቆራጠን መደበቅ ነበረብን፡፡ ድንጋይና የቦምብ ፍንጣሪዎች በሚያሰገርም ፍጥነት እያፏጩ ወደ መጠሰያችን ይመጡ ነበር፡፡ ጭሰና እቧራ መተንፈሻችን ሰለዘጋው ያደረግነውን ጭምብል ለማውለቅ ተገደድን፡፡ የማይቻል ድካም ይሰማን ጀመር፡፡ በነበረን የሰውነት እቀማማጥ ምክንያት መጋጠሚያዎቻችን ላይ ቁርጥማት ጀመረን፡፡

ወዲያውኑ የሸሰቆው ግማሹ በጨለማ ተዋጠ፡፡ ፀሐይዋ ጥቅጥቅ ባለ እቧራና ጭሰ ተጋርዳለች፡፡ የወንዙ ውሃ ከተራራ የወጣ ፍል ውሃ ይመስል መጨስ ጀመረ፡፡ ሙቀቱ የሚቻል እልነበረም ሁሉም ነገር የቃጠሎ ሽታ ነበረው፡፡

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አውሎ ነፋስ ተነሳ፡፡ በፍጥነት እየጋሰ የመጣው የእካባቢ ሙቀት የአየር ማዕበል መፍጠር ጀምሮ ሰለነበረ እውሮፕላኖቹ ተመልሰው ጠፉ፡፡ .

ለሰዎቹ ፀሎታቸው መልስ አገኘ፡፡

በተረፈው ቀን የሚመጡት እውሮፕላኖች ተመልካቾች ብቻ ነበሩ፡፡ መንገደኛው ሀሳቡን ሳይቀይር ቀጥታ ወደ ቤቱ ብቻ የሚጓዝ መሆኑን ማረጋገጥ ፈልገዋል፡፡

"እልቂት" በዛን ቀን ሰደረሰው የቦምብ ድብደባ ምናልባትም የሚሰማማው ቃል መሆን እሰበት፡፡ ግማሽ ሰአት ያክል እንኳን እልቆየም ነገር ግን ጦሩ የሞት እይቀጡ ቅጣት ነው የደረሰበት፡፡ ከዚህ በኋላ ማንም በጭራሽ ጣልያኖች ላይ ሙከራ እያደርግም፡፡ የባዶሊዮ ስሌት ነበር፡፡



እሰቃቂና ኢሰብእዊ ያም ሆኖ ምህረት የለሽ በሆነ ሁኔታ ስሌቱ ትከክለኛ ነበር፡፡ የደከመው ወኔና ስሜት በጠቅላላ በነዚህ የነጎድጓድና የመብረቅ አምላኮች ፍራቻና እከብሮት ተተካ፡፡

የራስ እምሩና የደጃዝማች አያሌው ጦር ያለ ምንም ጥርጥረ ተሸነፈ፡፡

በግድያው ቦታ የሚታየውን መግለፅ የሚያዳግት እሳዛኝ ነገር ነው፡፡ የቆሰሉ ሰዎች ውሃ ውስጥ ወይም ዳርቻው ላይ ተቀምጠዋል፡፡ እንዳንዶቹ ጥማቸውን ሰመቁረጥ ይሞክራሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ በእፈርና በረጋ ደም የተሸፈነውን ቁስላቸውን ያጥባሉ፡፡ በዚህም በዚያም የተበጣጠሰ የሰው እስከሬን ይታያል፡፡ ውሀ ውሰጥ ደግሞ የሞቱ በቅሎዎች ከነሸከማቸው ወይም ያለሸከማቸው ወድቀው ይታያሉ፡፡

በጠቅላላው መንገዱ ላይም ተመሳሳይ ሁኔታ ነው የሚታየው ልብ የሚያሰጨንቅ የእርዳታ ፀሎትም ይሰማል፡፡ የጦሩ ሙሉ ሰንቅ ተደምሰሷል፡፡ በየመንገዱ የዱቄት ክምር፤ ማር፤ ቅቤ፤ እህል የማብሰያ እቃዎች ልብሶች በየቦታው ተበትነው ይታያል ባዶ ሳጥኖችም ቢሆን በእሳት እየነደዱ አብረው ተበትነዋል፡፡ የሞቱ በቅሎዎች፤ ፈረሶች እና እህዮች ከምር አልፎ እልፎ ከሚታይ የሰዎች እስከሬን ጋር ተደባልቆ ከገደሉ ስር ይታያል፡፡ እንዳንድ እንስሶች መንከባለል ሲጀምሩ ሌሎችንም ይዘው ሲወርዱ እንደ ናዳ ፈጥረው ታች ዝቅ ያለው ቦታ ላይ ሲደርሰ ነው የቆመው፡፡

እንድ የበታች መኮንንና ጥቂቶች ወታደሮቹ ፊታቸው በሸማ ተሸፍኖ ከዛፍ ግንድ ተጠግተው ተደግፈዋል፡፡ ሁሉም የሞቱ ነበሩ፡፡

ቆንጆ የሆነች ሴት ድንጋይ ተደግፋ ተቀምጣለች፡፡ ያደረገችው ጥቁር ባርኔጣ የትልቅ ሰው ቤተሰብ መሆኗን ያሰታውቃል፡፡ እንደ እመድ የገረጣው ፊቷና የጎደጎዱ አይኖቿ ያሳለፈችውን መከራ ይገልፃሉ፡፡ ምን ሆነሽ ነው ተብላ ስትጠየቅ ቀሚሷን ነበር የምትገልበው፡፡ ግራ እግርዋ ከጉልበቷ በታች ተገንጥሎ የለም ደም እንዳይፈሰ ጭኗ በመቀነት ጥብቅ ብሎ ታሰሯል፡፡ ጓደኞቿ የሉም፡፡ ምናልባትም እነሱም ሞተው ይሆናል፡፡ በእባቷ አስከሬን እጠገብ ተቀምጣ ታነባለች፡፡

እይን የሚያየውን ይህን ሁሉ አሰቃቂ እይታ ማነው መግለፅ የሚችለው? ብዙ ባለጌዎች እጋጣሚውን በመጠቀም ቦምብ በሚጣልበት ጊዜ ከሚበተኑ ጭነቶች ላይ ውድ እቃዎችን ይሰርቁ ነበር፡፡ ገንዘብ የሆነ ወይም ገንዘብ ነከ

የሆነ ነገር መጀመሪያ ይወሰዳል። እንደሚባለው ከሆነ ብዙዎቹ ለመስረቅ ሲሻሙ እርስ በርስ ይተኳኮሱ ነበር።

ራስ አምሩ የነበራቸውን ሁሉንም ነገር ነው ያጡት። ልብሳቸው፣ ቀለባቸው ሌላውን ጨምሮ የተረፋቸው ሀያ ሁለት ሺ ብር የለም። ደጃች አያሌው ደግሞ አምስት ሺ ማር ትሬዛ ብርና ሌሎችም ነገሮች ጠፍተውባቸዋል።

እኔም ብሆን የራስ አምሩ ዕጣ ነው የደረሰብኝ። የነበረኝ ሁሉ ነገር መድሃኒቶችን ጨምሮ በእሳት ነው የተቃጠለብኝ። የነበረኝ ሀያ ሺ ሊሬም ሄዷል። በተጨማሪ ምትክ የሌላቸው ሰማንያ ስድስት የፎቶ ፊልሞች (ነጋቲቭስ)፣ ትልቅ ማሰታወሻ መፃፊያ፣ የመንገድና የመኝታ ልብሶቼ ሌሎችንም ጨምሮ። አሁን ያለኝ የለበስኩት ልብስ ብቻ ነው። ከዚህ ሁሉ ግን ትንሽ ማሰታወሻዬንና መፅሐፍ ቅዱሴን ማዳን ችያለሁ።



# ምዕራፍ ሀያ

## በሰሜን ተራሮች ላይ

ወደ ላይ ፀጥ ወዳሉት በደመና በተሸፈኑት ወደሰሜን ተራሮች እናቶች ሽሽቱ ቀጠለ። አሁን ትዛዙን የሚሰጡት ተራዎቹ ሰዎች ናቸው። የጦሩ አዛዦች ያለምንም ሥልጣን መከተል ብቻ ነው የነበረባቸው። ለደህንነትም ሲባል አዛዦቹ በማታ ብቻ ነበር የሚጓዙት።

እውሮፕላኖቹ የቅስቀሳ ወረቀቶች በተከታታይ ይበትኑ ነበር በወረቀቱም ጣልያኖቹ ከተራው ህዝብ ጋራ ምንም አይነት ጠብ እንደሌላቸው ይገልፁ ነበር። መቅጣት የሚፈልጉት የንጉሡ ተከታዮች የሆኑትንና ገበሬውን የሚያሰቃዩትን የጦር መኮንኖችን ብቻ ነው። ስለዚህ ተራው ሰው ወደየቤቱ በእስቸኳይ እንዲመለስ ተማሳፅም ይሰጡ ነበር። ይህንን ትዛዝ ከተቀበሉም ከድብደባ ይድኑ ነበር።

ከዚያ በኋላ የቦምብ ድብደባው በጣም እልፎ አልፎ ነበር የሚካሄደው። በምብም የሚጣለው አንድ ካምፕ ከአንድ ቀን በላይ የሚቆይ ከሆነ ጥርጣሬ ካለ ነው። ያም ሆኖ ግን እውሮፕላኖቹ ከፊት ለፊት ከሚሸሸው ሰው መንገድ ዳርና ዳር የሚገኘውን ሳር በሙሉ በእሳት ያቃጥሉት ነበር። መንገዳችንም በረሃብና በድካም ምክንያት የሞቱ በመቶዎች የሚቆጠሩ ፈረሶች ይታይበታል።

ከአበር ተራራ ስር ለሁለት ቀናት እቆምን። ማምሻውን በመጣ ዜና የጣልያኖች ሬጅመንት እኛ ያቋረጥን ቀን ተከዜን ማቋረጡን ሰማን። ነገር ግን ከኛ ዝቅ ብሎ ነው የተሻገሩት። አሁን ደግሞ ወደ ዳባት እየተጓዙ መሆናቸውን ሰማን። ራስ እምሩ ወደ ግንባር ሲመጡ ይዘው የመጡትን መንገድ ይዘው ነው ወደ ዳባት የሚሄዱት። የካምፕ እሳታቸውን ከታች ከረባዳው መሬት በምእራብ በኩል እሥራ እምስት ኪሎ ሜትር በማይሞላ ርቀት ማየት እንችል ነበር።

በጣም ተዝናንተዋል ምንም እንግዳ በሆነ በጠላት ቦታ ቢሆኑም ግን ቀድሞ ዳባት ይደርሳል በሚል አይተፎካከሩ ነበር።

ራስ እምሩ ጣልያኖችን ለማዘግየት ማጥቃት ፈልገው ነበር ነገር ግን ወታደሮቻቸው ፊት ለፊት ትዛዙን እንደማይቀበሉ አስታወቁ:: እንደ ወታደሮቹ ግዛቱ የዳኛማች አያሌው ስለሆነ የመከላከል ሀላፊነቱም የሳቸው እንጂ የነሱ አይደለም:: ወደ ቤታቸው በተቻለ መጠን በፍጥነት መመለስ ሰለወሰኑ ራስ እምሩ ከፊለጉ መከተል አለዚያም መቅረት ይችላሉ::

በሌላ በኩል ደጃች አያሌው በሶስት ፊታውራሪዎች የሚመራ አምስት መቶ ወታደሮች ማሰባሰብ ችለው ነበር:: ትዛዙም በማታ ጠላትን በማጥቃትና በመረበሽ ወደኋላ መመለስ እንዲያስብ ለማድረግ ነበር:: በተጨማሪም ወታደሮቹ ገበሬዎች ጠላት እንዲራብ ለማድረግ ቤታቸውን ባዶ እንዲያደረጉ ይገፋፉ ነበር:: እንደ ሰማነው ከሆነ ጠላት ስንቅ ሳይዝ ነው የተንቀሳቀሰው፤ የሚፈልገውን ነገርም ከገበሬዎች እየገዛ ነበር::

አንድ ቀንም አለፈ በሁለተኛው ቀን ከሰአት በኋላ አንደኛው ፊታውራሪ ከሰላሳ ሰዎች ጋራ ተመለሱ:: ወኔያቸው የወደቀ ይመስላሉ:: ምን ተፈጠረ?


ሁለቱ ፊታውራሪዎች የኛ ማጥቃት ተስፋ የሌለው ነገር ነው ብለው ከቀረው ጦር ጋር ከጣልያኖቹ ጋራ ተደባልቀዋል::

ይህ የመጀመሪያው ከዳት ነበር:: ደጃዝማች አያሌው ላይ ከፍተኛ የሀዘን ስሜት ነው የፈጠረው:: የዚህ ላይበቃ ደግሞ በደረሳቸው ደብዳቤ በዳባት የገበያ ቦታውና የገብርኤል ቤተክርሰቲያን በአየር ድብደባ ወድመዋል::




በዳባት ከተማ ተመልሶ የተሰራው የቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን






በዳባት አሁንም የሚገኝ ቤተክርሰቲያኑ ላይ ከተጣሉ ቦምቦች የአንዱ ከፍል

ከዚያን ቀን በኋላ ደጃች አያሌው እንደድሯቸው አልሆኑም:: ከዚህ ቀደም ተጫዋችና ተደባላቂ የነበሩት ሰው ዝምተኛና ቀስተኛ ሆነዋል:: ፀጉራቸው አልፎ አልፎ ሽበት የነበረበት በጥቂት ቀናት ውስጥ ተቀየረ:: በሙሉ ነጭ ሆነ::

ይህ ሁሉ ችግር እያለ ሁሉም ነገር አለቀለት የሚለውን አሰተሳሰብ ግን አልተቀበሉትም::

ውሳኔውም በተቻለ ፍጥነት ከዳባት ሰላሳ ኪሎሜትር ርቀት ወደሚገኘው የደጋው ከተማ ወደ ደባርቅ እንድንሄድ መንገዱም ለማለፍ አሰቸጋሪ በሆነው በሊማሊሞ ገደል በኩል እንዲሆን ምክንያቱም ጣልያኖቹም ማለፍ የፈለጉት በዚሁ በሊማሊሞ በኩል ሰለሆነ ነበር:: የዚህ ማለፊያ ለሀምሳ ሜትር የሚሆን ቦታ ላይ በጣም ጠባብ ሰለነበር የተጫነ አህያ ማለፍ አይችልም ነበር:: እዛ ቦታ ላይ በጥቂቱ በመቶ የሚቆጠሩ ሰዎች ቦታ ይዘው ለማለፍ የሚሞከረውን ማንኛውም ጠላት እንዲያሰቆሙ ታሰበ::


ትዛዙም ለፊታውራሪ ተሻገር ተሰጠና ወታደሮች ይዘው በአስቸኳይ ወደ ሊማሊሞ ማለፊያ እንዲሄዱ ነበር:: ከአየር ድብደባ የሚከላከሉበት መጠለያ እንዲያዘጋጁ በተጨማሪም ጠመንጃ መደገኛ ጉድቦች እንዲቆፈሩና ወደ ረባዳው መሬት አቅጣጫ ሁለት ቦታ ላይ ግንብ እንዲገነባ ተወሰነ::




በዳባት ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ የሚገኝ
ደጃዝማች አያሌው ራሳቸው ያሰሩት የመቃብር ቤታቸው

በዚህ ጊዜ እኛም በአሰቸጋሪ ሁኔታ ወደ ላይ ወደ ተራሮች መውጣት ቀጠልን፡፡ ሁልጊዜ ወደ ላይ መውጣት ነው፡፡ አየሩም በየቀኑ እየቀዘቀዘና እየቀሰሰ ይሄዳል፡፡ መያዝ የቻልነውን ወሰድን ከነልብሳችንም እንተኛ ነበር፡፡ ምንም ነገር አልነበረንም፡፡






የደጃች አያሌው መቃብር ቤት በሌላ ጎን ሲታይ

የቅማል ነገር እንዴት ነው ብሎ ሰው ሊጠይቅ ይችላል፡፡ አዎ ቅማል ነበር፡፡ እነዚህ ትንንሽ ተባዮች ሰዎችን እንደዚህ ያስቃያሉ ብዬ ገምቼ አላውቅም፡፡ የሚገርም ነው በአንድ ወቅት በአውሮፓ የነበሩ መርማሪዎች (ኢንኩዊዝተርስ) ቅማሎችን ሰው ለማስቃየት አለመጠቀማቸው፡፡ ስንት አንቅልፍ ያጣሁባቸው ማታዎች ነበሩ በበሉኝ ቁጥር እንደ ህፃን ልጅ ያስለቅሱኝ ነበር፡፡ በማከክ ብዛት ቆዳዬ ተልጦና ቆስሎም ነበር፡፡ በመጋቢት ሶስት በማስታወሻዬ የሚቀጥሉትን ቃላት ስፅፍ ስለቅማሎቹ እያሰብኩ ነበር፡፡

ከየካቲት ሀያ ሶስት ውጊያ በኋላ ከፍተኛ ስቃይ ነው የደረሰብኝ::
አሁንስ ሁሉም ነገር ደከሞኛል፡ ምናለ ማቆሚያ ቢኖረው

አንድ ቀን አቶ ማሞ ወደ ዋሻችን መጣ በጣም የተጨነቀ ይመስላል:: ልጁ አፀደ ለሁለት ቀናት አልታየችም:: የራስ እምሩ ሰዎች ሰርቀዋታል ብሎ እርግጠኛ ነበር:: ምክንያቱም በዚያ በመበታተኑ ጊዜ በአንዳንድ የራስ እምሩ ወታደሮች ዘንድ ፈረስ በቅሎና አገልጋዮች መስረቅ የተለመደ ነገር ሆኗል:: ሀሳባቸውም በየትውልድ ቦታቸው ተመልሰው ሲገቡ ለመሸጥ ነው::

አሷን እንዴት እንደምንፈልግ እየተነጋገርን እያለን አንድ ወታደር ይዟት መጣ:: እንደ ወታደሩ አገላለፅ አንድ ቀን በንጋቱ ገና ጨለማ እንደሆነ አፀደን በአንቅልፍ ልቧ ወደሱ ስትመጣ ያያታል:: ከንድዋን ሲጨብጥ ነቃች ደንግጣም ነበር ነገር ግን የማስታወስ ችሎታዋ እንደጠፋ ይረዳል:: ልጅቷ የራሷን ስም ሆነ የወላጇቿን ስም ማስታወስ አልቻለችም:: ያን ቀን ብቻ የሚያውቃት ሰው መጥቶ የአባቷን ስም ሲጠራ ማስታወስ ጀመረች::

መልካም ያ ጥሩ ነገር ነበር!! ከዚያ ውጭ ግን በዚህ በማይረሳ መከራ ቀን አንድ ጣጣ በሌላ ጣጣ ይተካ ነበር::

ፈጠነ በጣም ታመመ የያዘው በሽታ ደግሞ የሚያገረሽ ተስቦ (Relapsing fever) መሰለኝ:: መድሐኒት አልነበረኝም በዚህ ያልሆነ ቦታ ደግሞ ጥዬው አልሄድም:: ደጃዝማች አንድ ከተከዜ ጭፍጨፋ የተረፈች በካምፑ ውስጥ ያለችዋን ብቸኛ በቅሎ ሳኩልኝ እኔም ፈጠነን አሳፈርኩባት:: መንገድ በጀመርን ቁጥር የትኩሳት ቅዠት ውስጥ ስለነበር እንዳይወድቅ ከኮርቻው ጋር በደንብ መታሰር ነበረበት::

መንገዱ ቀጥታ በሰሜን ተራሮች በኩል ነው የሚወስደው:: ሲያደናቅፈኝ በአይኔ ብልጭታ ማየት ጀመርኩ ጉልበቶቼም ሊከዱኝ ያሰቡ ይመስላል:: የምግብ ዕጥረት ከቅማሎቹ ደም መምጠጥ ጋራ ያሰኘን አቅም በሙሉ አዳከሞታል::

ከብዙ ቀናት በኋላ ከታች ከተከዜ ሸለቆ ከባህር ወለል ዘጠኝ መቶ ሜትር ከሆነ ቦታ ጀምረን ወደ ላይ ከባህር ወለል አራት ሽ ሜትር ከፍታ በላይ ወጥተናል:: እዚህ ላይ ባለግርማ ሞገሱ ቡዋሂት በአራት ሺ ስድስት መቶ ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል:: ከብዙ አመታት በፊት ይህ ተራራ በወንድሜ በዋልደማርና በጂኦሎጂስቱ ዶክተር ኤሪክ ኔልሰን ድል ተደርጓል::



ሁለቱ በአቢሲኒያ ከፍተኛው ተራራ ላይ እግራቸውን ለማሳረፍ የመጀመሪያዎቹ አውሮፓውያን ነበሩ:: ኩርምትምት ብዬ ቁጭ ስልና በበረዶ የተሸፈነውን የተራራውን ነጭ አናት ስመለከት የቫይኪንግ ትውልድ ያላቸው ስውዲናውያኑ እንደወንድሜና ዶክተሩ ያሉ ጠንካራ ሰዎች ናቸው እንዲህ ያለውን ነገር መፈፀም የሚችሉት አልኩኝ:: ሌላ ሰው ተራራው ጫፍ ድረስ ለመውጣት ገና መቆየት አለበት ብዬ አሰብኩ:: ስዊድን ለዘላለም ትኑር!

ይህ ግርማ ሞገስ ያለው አስደናቂ አይታ መንፈስን የማደስ ስሜትም ይፈጥራል:: ላፍታ ያክል የወንድሜን እግር የመከተል ስሜት ተፈታተነኝ:: አቢሲኒያኖችን ስውዲናዊ ማድረግ የሚችለውን ነገር ባሳያቸው ደስ ባለኝ:: የዋልደማር ወንደምስ አይደሰሁም ወይ? እያሌውና ሰዎቻቸው በደምብ የሚያውቁት ዋልደማር! ሙሉ አድናቆታቸውን ያገኘው ዋልደማር::

ነገር ግን በታው በጣም ቀዝቃዛና የሚቆረጥም ብርድ አለው:: መሬቱ እንደበረዶ ቀዝቅዞአል እዚህ እዚያም የበረዶ ክምር ይታያል:: ስሳ ያለው አየር ትንፋሼን ቁርጥ ነው ያስደረገኝ ብስበው ብሰበው የሚበቃ አየር የማገኝ አልመሰለኝ አለ:: ከጂባራውና(ጅብራ) እጅብ ብሎ ከሚታያው ከርዳዳ ሳር ውጭ ሌላ አይነት ተክል አይታይም:: ጅባራ የሚገኘው ከባህር ወለል ሶስት ሺ ስምንት መቶ ሜትር ከፍታ ብቻ ነው:: ቁመቱ እስከ ሶስት ሜትር ድረስ ይሆናል ከሩቅ ሲታይም ልክ የዘንባባ ዛፍ ይመስላል:: ከስር በኩል ግንዱ የሀያ አምስት ሴንቲ ሜትር ውፍረት አለው ወደ ላይ እያደገ ሲሄድ ግን መቅጠን ይጀምራል:: ተክሉ ሲደርቅ እንደ ግንድ ነው የሚነደው ነገር ግን ሙቀት አይሰጥም::

በቡዋሂት ምእራብ ጎን በኩል ባለ ዋሻ ለሶስት ቀናት ሰነበትን:: በዚህ ቦታ ብዙ በጎች ይረባሉ:: አንድ በግ በርካሽ በሀምሳ እር (ግማሽ ክራውን - የስዊድን ገንዘብ) ይገዛል:: ጉልበታችን ማገገም የሚችልበት ቦታ ነው ብለን አሰበናል::

ከጥዋት እስከ ማታ በግ በየተራ እያታረደ ይቀቀላል:: እንደዚህ ጊዜ ስጋ በብዛት በልቼም አላውቅም ይህን ያህልም ቡቡኝ ጠጥቼ አላውቅም:: ለመጀመሪያ ጊዜ ምን ያህል ተርበን እንደነበር ተገነዘብን:: ጨጓራና አንጀታችንም አልተጣሉንም:: ምን ያህል ብዛት ቢኖረውም የበላነውን ሁሉ ተቀበሉ::

የሰሜን ገበሬዎች እነዚህ ትሁትና የደጋ ተራ ሰዎች በግልፅ ወዳጅ መስለው ነበር የሚታዩት:: ሲመጡም አንጨት ጠላ ዳቦ ወተትና እህል ስጦታ ይዘው ነበር:: እልፎ አልፎም አንቁላል ይሰጡን ነበር:: አገሩ ግን የዶሮ ሀብት የለውም::

ካምፑን ለቀን በምንሄድበት ቀን በጥዋቱ ገላየን ታጥቤ በፈላ ውሃ የተቀቀለ አዲስ ልብስ ከለበስኩ በኋላ  በጣም ደሰታ ተሰማኝና ከደጃዝማች ልጅ ጋራ በመሆን ዋልያ ለማደን ወጣን:: ዋልያ በሰሜን ብቻ ነው የሚገኘው:: ብዙ ዋልያዎችን ቀጥ ባለው ገደል ላይ አየን:: ጠጋ ብለን ለመተኮሰ የጠመንጃ ተኩስ ርቀት ያህል የሚያሰጡን አይነት አልነበሩም:: በተጠጋን ቁጥር ስለሚሸሹ አፋራምነታቸውን አስመሰከሩ:: ለማንኛውም እንዲህ አይነት ያልተለመደ አደን ለማድረግ ወጥተን ነበር::

በሳንቃ በር በኩል አድርገን ወደ ደባርቅ መንገድ ቀጠልን:: ሳንቃ በር በዚህ ቀጥ ባሉ አለትና መጋጠሚያዎች በተከበበው ሰሜን ክልል ካሉት ሶስት ማለፊያዎች አንዱ ነው:: የጣልያን ወታደሮች ከታች ከደልዳላው ቦታ ስለተቀመጡ እኛ የሚሻለን በዳባትና በደባርቅ መሀከል ግማሽ መንገድ ላይ በሚገኙ ዋሻዎች ቆይተን የሚመጣውን ማየት ነው ብለን ወሰነናል::

እሁን የደረስንበት ዋሻ ትልቅ ነበር በቀላሉ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎች ማስተናገድ ይችላል ነገር ግን በእርጥበቱ ምክንያት ውስጡ መቆየት የማይቻልበት ሁኔታ ደረጃ ሊደርስ ይችል ነበር:: ሰፊና ጠመዝማዛ መንገድ በተራራው መሀል ለመሃል ይወስዳል:: ለደቂቃዎች ከተጓዝን በኋላ  ሰፊ ውሀ የተከማቸበት ኩሬ ደረስን:: ውሀው ከላይ አንደነጎድጓድ እይጮኸ በሚወርደ ፏፏቴ ይሞላል:: በፏፏቴው ጩኸት ንግግሬ መሰማትም አይችልም ነበር:: ኩሬው ከስር በኩል የውሀ መውጫ ቢኖረው ነው እንጂ ከላይ በኩል የሚታይ የውሀ መውረጃ አይታይም ነበር::

ከሳንቃ በር ወዲህ ከአቶ ማሞና ቤተሰቦቹ ጋራ በጣም ተቀራርቤያለሁ:: ከነሱ ጋራ ሆኜ የሚቻለውን ቦታው የሚፈቅደውን እንክብካቤ አግኝቼአለሁ:: በቀሩት ወራቶች አብረን ነው ያሳለፍነው:: ከደጃዝማች በየቀኑ የሚላከልንን ዳቦ አንደወንድማማች እንከፋፈል ነበር::

ደጃች አያሌው በቆየ ቁጥር ዝምታቸው እየጨመረ ነበር የሄደው:: ጨዋታቸው ምንም አልተሻለም ያ ግን የራስ ካሳ ልጅ የሆኑት ባለቤታቸው ከዳባት ተነስተው እኛን ለመከተል እስኪመጡ ድረስ ነበር::



ባለቤታቸው ስማቸው ማናህሎሽ ነበር ሲመጡም የውጭውን አለም ጭልፍታ ይዘው ነበር የመጡት:: በጣም ንፁህ ናቸው ለብዙ ጊዜ አዲስ አበባ ሲኖሩ እንደ አውሮፓዊ ባላባት ሴቶች ነበር የኖሩት ያም በባህሪም በአለባበስም ጭምር ነበር:: በጣም መልከኛና አስደሳችም ነበሩ ነገር ግን ራስ ወዳድ በመሆናቸው የተነላ ተወዳጅነት አልነበራቸውም:: ይህ ባህሪ ደግሞ የተወረሰ ነው ተብሎ ይወራ ነበር:: በሳቸው እርዳታ ነበር አስቀያሚና የማይመቸውን ፂሜን ማስወገድ የቻልኩት:: ፂም መላጫዬንና ሌሎች ንብረቶቼ ተከዜ ላይ ስለጠፉብኝ ፂሜን ከማላደግ በስተቀር አማራጭ አልነበረኝም:: ከነበራቸው የመዋቢያ ነገሮች ጋራ ፀጉር የሚያስወግድ ወይም የሚነቅል ፓውደርም ይዘው ነበር:: በወፍራሙ ፂሜ ላይ አደረግሁበት ከሶስት ደቂቃ በኋላ  ፂሜ አንደ ህልም ድራሹ ጠፋ:: ደስተኛ ነበርኩ:: ከዚህ በኋላ  ግን ደግሜ ተጠቅሜ አላውቅም::




ደጃች አያሌውና ባለቤታቸው ወይዘሮ ማናህሎሽ ካሳ (Agenore Frangipani)

በዚህ ትልቅ ዋሻ ሶስት ቀናት እንዳሳለፍን ፈታውራሪ ተሻገር በላብ ተጠምቀው ፈረሳቸውን እየጋለቡ መጡ:: ሰዎቹ ከድተዋቸዋል እናም ብቻቸውን የሊማሊምን ማለፊያ መከላከል አልቻሉም::

ጣልያኖቹ በደባርቅ ከተማ ዙሪያ ካምፕ መስርተዋል:: የአካባቢው ገበሬዎች በሙሉ ለኛ ግልፅ የሆነ ጥላቻ እያሳዩ ነው:: ለጣልያኖቹ

ወዳጅነታቸውን ለመግለፅ ሁሉም ነጭ ባንዴራ በየጎጆአቸው ላይ ያውለበልቡ ነበር፡፡ በገበሬዎችና በወታደሮች መሀከል ተኩስ ልውውጥ ማድረግ የተለመደ ነገር አየሆነ መቷል፡፡ ፊታውራሪ ደግሞ የነበራቸውን ጥሩ ዜናም ማካፈሉን አልረሱም ነበር፡፡ የጣልያን አውሮፕላኖች በስህተት የራላቸውን ሰዎች በቦምብ ደብደው በራሳቸው ዜጎች ላይ ሞትና ሽብር ፈጥረዋል፡፡

ወዲያውኑ የተወሰነው ውሳኔ ደጃች አያሌው ራላቸው ብቻቸውን ወይም ከኛ አምሳት ኪሎ ሜትር ርቀት ከሚገኙት ራስ አምሩ ጋራ በመሆን ጣልያኖቹን ለመመከት ነበር፡፡ አቶ ማሞ እና እኔ ራሴ ከሌሎች ሰዎች ጋራ በመሆን የተሰጠን ሀላፊነት ወይዘሮ ማናህሎሽን እጅብን በቀጥታ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ እንድንሄድ ነው፡፡  ሀሳቡ በሱዳን በኩል አድርገን ሄደን ከአንግሊዞች መጠለያ ለማግኘት ነው፡፡ ደጃዝማችም በሙከራቸው ካልተላካለቸው አኛን ሊደርሱብን እንደሚሞከሩ ነበር፡፡

ከሰአት በኋላ  ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት ላይ ደጃዝማች ከብዙ መቶ ሰዎች ጋር በመሆን ተለይተውን ሄዱ፡፡ እኛ ግን መንገድ ለመጀመር የጨረቃ ብርሃን እሰኪወጣ ድረሰ መጠበቅ ነበረብን፡፡ ልክ አንደ ሌሎቹ ሴቶች ሁሉ ወይዘሮ ማናህሎሽ በፍፁም ተዘጋጅተው አልጨረሱም፡፡ ይሄ ጎድሏል፤ ልብሱ በደንብ ሳከት አላለም፤ ጫማው ይቆነጥጣል ወይ ደግሞ የፀሐይ ባርኔጣው ቀለም ከሌላው ጋራ የሚለማማ አይደለም፡፡

እንደ ተለመደው መንገዱ በጣም አለቸጋሪ ነበር ዕጣችን በሙሉ በአሰቸጋሪ መንገዶች እንድንጓዝ የተወሰነበት ይመሰላል፡፡ አንድ ሰባት የሚሆኑ አላዛኝ ሁኔታዎች ወደ ሰምንት አሰቸጋሪ ሁኔታዎች (ከሌሎች ሁኔታዎች ጋራ የአቶ ማሞ ፈረሰ ከነጭነቱ በገደሉ ወድቆ ቀርቷል) በኋላ  የሚያምርና እሰደናቂ ወደ ሆነው ̈የቦዛ አካባቢ ደረሰን፡፡ አዚህ ቦታ ላይ ሆነን በሰምምነታችን መሰረት የደጃዝማቸ አያሌውን ወሬ ልንጠብቅ ነው፡፡

አኩለ ቀን ሲሆን ዜና መጣልንና ከነበረን መዳከምም እንድንነቃ አደረገን፡፡ በዙሪያው በነበሩ ሰዎች ግን ከፍተኛ ጩኸት ነበር፡፡ የደጃች አያሌው ሁሉም ንብረት ዳባት አጠገብ ባሉ ዋሻዎች ተደብቀው ነበር ነገር ግን በአካባቢው ሰዎች አንዳለ ተዘርፈዋል፡፡ ሁሉም አርሰ በርሱ አየተራኮተ ነበር፡፡ እቅም ያነሰው ለባለጉልበተኛው መልቀቅ ነበረበት፡፡ ይህ ሁኔታም በየቦታው የሚታይ ነገር ሆኗል፡፡



ራስና ደጃዝማች ለኛ የሚበጀው ወደ ጎንደር መሄድ ነው ብለው አሰበዋል ለለዚህ እኛም ከኋላቸው ወደ ረባዳው በሚወሰደው መንገድ ላይ እንድንደርሰባቸው ተወሰኖአል፡፡ ሰባት ሰአት ሲሆን መንገድ ጀመርን መንገዳችንም ለሰሰት ቀናት ቀጠለ በመሀል የዘጠኝ ሰኢታት አረፈት ብቻ ነው ያደረግነው፡፡

በመጨረሻም ደንቀዝ የሚባል ከተማ ደረሰን፡፡ ፀሀዩ ያቃጥላል እሰኪመሸ ድረሰና ከአምሰት ወራት በፊት ወደ ጠገዴ ስሄድ የመጣሁበትን መንገድ እሰከምናቋርጥ ድረሰ የሚጠጣ ውሀም አላገኘንም፡፡ ሌሊቱ አንዳለፈ ፀሀይ ሰትወጣ ወደ ሰማይ ቀጥ ብሎ የወጣ የመቶ ሜትር ከፍታ ያለው ዳገት መውጣት ነበረብን፡፡



በዳባት የሚገኝ የደጃች አያሌው ግብር ማብያ ቤት የነበረ (ደሳለኝና ገበየሁ)



በዳባት የደጃች አያሌው
ፍርድ መስጫ ሥፍራ
የነበረ

ደጋማው ቦታ ላይ እያለን በቡድን በተደራጁ ገበሬዎች ጥቃት ደረሰብን ሆኖም ከሀያ ደቂቃዎች ውጊያ በኋላ በነበሩን ሶስት አውቶማቲክ መሳሪያዎች እርዳታ ልናባርራቸው ቻልን፡፡

ከለእት በኋላ ሲሆን ራሰና ደጃዝማች ይጠብቁን ስለነበር ደረሰንባቸው፡፡ የማውቃቸው ጓደኞቼንም አገኘሁ፡፡ ከአዲስ አበባ ከመጡ ሁለት የአቢሲኒያ ፓይለቶች ጋራ ተዋወቅሁ፡፡ አውሮፕላናቸው ዳባት ላይ ስለተመታ ከእጀቡ ጋራ በመሆን ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ ወስነዋል፡፡

ከምሽቱ ሶስት ሰእት ሲሆን በፀጥታና በተረጋጋ ሁኔታ በጣም ደስ በሚል ጨረቃ ብርሃን ስር ወደፊት እንጓዝ ነበረ፡፡ ድንገት ተኩስ ከሁሉም አቅጣጫ ይተኮስብን ነበር ጥይቶችም እያፏጩ በአናታችን ላይ ይበሩ ጀመር፡፡ ግራ እንደገባው ዶሮ በየቦታው በጭንቀት የሚሮጡት ህፃናት ለመከላከልና ለመደራጀት አሰቸጋሪ ሁኔታ ፈጠሩብን፡፡ እንስሶችም ፈርተው ስለነበር ችግሩን አባባሱት፡፡

ተኩሱ ቀስ እያለ እየጨመረ ሄደ የኛም አውቶማቲክ መሳሪያዎቻችን ተጠመዱና መንጣጣት ጀመሩ ወታደሮቻችን በጨለማው ወደማይታይ የጠላት አቅጣጫ ነበር የሚተኩሱት፡፡

"እሃ! ተመልከት!" ከመትረየስ ተኳሾቹ አንዱ መሳሪያውን ወደኛ አዞረብን፡፡ ጥይቶቹ በአናታችን ላይ ነው የሚሄዱት ግን ይሄ ከሀዲ መትረየሱን ወደ ታች ማነጣጠር መቼ እንደሚጀምር ማንለ ያውቃል?

"እበራ! እንዳትለቀው!"

ደጃማች ነበሩ ለአነጣጥሮ ተኳሻቻው ትዛዝ የሰጡት፡፡ አበራም በርከከ አለና ጠመንጃውን ከጉንጬ አስጠግቶ ተኮሰ፡፡ ኢላማ! መትረየሱም ፀጥ አለ ተኳሹም ወደ መሬት አጥፍ አለ፡፡ ከግማሽ ሰእት ተኩስ በኋላ አጥቂዎቻችን ሙትና የቆሰሉ አስር ሰዎቻቸውን ትተው ተበተኑ፡፡ እኛ ግን በአጥፍ የሚሆን ነበር ያጣነው፡፡

መንገድ እንደገና ለመጀመር ስንዘጋጅ አንደኛው የኢጣልያ አስረኛ የለም፡፡ በየቦታው ተፈልጎ በመጨረሻ ዋሻው ውስጥ ተገኘ፡፡ በዚያው እንደተደበቀ እንቅልፍ ወስዶታል፡፡ ሙሉ ቀን ያላለፊው ጉዞ አድከሞትም ነበር፡፡

በመንገዳችን ላይ የሚደረሰብንን ብዛት ያለው ጥቃት መቋቋም ነበረብን፡፡ ጉልበታችንን ጨርሰን በመጋቢት ሀያ ሁለት እንድ ጥንታዊ ፍርሥራሽ ያለበት ደንቀዝ ከተማ ገባን፡፡ እዚህ እያለን የሚገርም ዜና ሰማን፡፡ ጣልያኖች ከአንድ



ቀን በፊት ጎንደር ከተማ ገብተዋል፡፡ እኛም ያለነው ከጎንደር አርባ ኪሎሜትር ርቀት ነበር፡፡ እንዴት እንዲህ ሊሆን ቻለ?

ጄኔራል ስታራቼ በሰምንት ቀናት ውስጥ ከሰቲት ተነሰቶ መንገድ እየሰራ መካናይዝድ የሆነውን ጦሩን ይዞ ጎንደር ሲገባ የምናውቀውም ነገር አልነበረም፡፡



በሰቲት በኩል ጎንደር ገሰግሶ የገባው ጄኔራል ስታራቼ
ከስር የሚታየው ጣልያኖች ጎንደር ከተማ ሲገቡ ነው

